# የኢ. ፌ. ዴ. ሪ ሕገ መንግሥት መሠረታዊ መርሆዎችና

# የፌዴራል ሥርዓቱ ልዩ ባሕሪያት

*በፌዴሬሽን ምክር ቤት*

*ለ6ኛው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን*

*ለውይይት የተዘጋጀ*

ኅዳር 2004 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# ማውጫ


ክፍል አንድ መግቢያ ........................................................................................3

ክፍል ሁለት የኢትዮጵያ የሕገ መንግሥት ታሪክ አጭር ዳሰሳ ........................................6

ክፍል ሦስት ................................................................................................17

የሽግግሩ ወቅት ቻርተርና የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ..............................................................17

ሕገ መንግሥት መጽደቅ ................................................................................17

ክፍል አራት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት ዓላማዎች፣ እምነቶች፣ መሠረታዊ መርሆዎችና ልዩ ባሕሪያት ................................................................................25

4.1. የሕገ መንግሥቱ ዋና ዋና ዓላማዎችና እምነቶች ........................................25

4.2. የሕገ መንግሥቱ መሠረታዊ መርሆዎች፣ ..................................................27

4.3. የብሔራዊ ፖሊሲ መርሆዎችና ዓላማዎች ..................................................42

4.4. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሕገ መንግሥት ልዩ ገጽታዎች ....................................48

ክፍል አምስት የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም፡ ህብረ-ብሔራዊ ፌዴራሊዝም ........................53

5.1. ሕገ መንግሥታዊ ዋስትና ያለው የስልጣን □□□ል መሠረት ያደረገ ፌዴራሊዝም ................................................................................54

5.2. ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦችን መሠረት ያደረገ ፌዴራሊዝም ...............62

5.3. የራስን ዕድል በራሱ የመወሰን መብትን መሠረት ያደረገ ፌዴራሊዝም ............66

5.4. በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ አንድነትን መሠረት ያደረገ ፌዴራሊዝም .........67

5.5. የተለየ የሕገ መንግሥት ትርጉም ሥርዓት የዘረጋ ፌዴራሊዝም .........69

5.6. የሕገ መንግሥት መሻሻል ሥርዓትን የዘረጋ ፌዴራሊዝም ..........................71

ክፍል ስድስት ማጠቃለያ ..................................................................................75

ዋቢ ጽሑፎች ..................................................................................................77

# ክፍል አንድ
## *መግቢያ*

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን ዘንድሮ ለስድስተኛ ጊዜ በመላ ሀገራችን፣ በውጪ በሚገኙ የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ አባላትና የኢትዮጵያ ወዳጆች ዘንድ *"ሕገ መንግሥታችን ለብዙሀነታችን፣ ለአንድነታችንና ለህዳሴያችን"* በሚል መሪ ቃል በታላቅ ድምቀት ይከበራል፡፡ የዘንድሮውን በዓል ልዩ የሚያደርጉት ምክንያቶች አሉ፡፡ የዘንድሮው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን የበዓል አከባበር በዓይነቱ ልዩ እንዲሆን ከሚያደርጉት ምክንያቶች ዋነኛው ታላቁ የህዳሴ ግድብ እንዲገነባ መሠረት የተጣለበትና የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ከፍተኛ መነቃቃትና ተሳትፎ በማድረግ ላይ ባሉበት ወቅት መሆኑ እና የአምስት ዓመቱ የእድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን ተግባራዊ ማድረግ በጀመርንበት ወቅት ላይ መከበሩ ነው፡፡ ስድስተኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን የሚከበረው ይህንን እቅድ ተግባራዊ በማድረግ የልማትና የዴሞክራሲ ጉዞችንን ለማስቀጠል ርብርብ በጀመርንበት ወቅት መሆኑ በዓሉን ልዩና ታሪካዊ ያደርገዋል፡፡

ዘንድሮም የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፌዴራላዊ ስርዓታቸው በጠንካራ መሠረት ላይ የተገነባ መሆኑን የሚያሳዩበት፣ በበገራችን በብሔር ላይ የተመሠረተ ጭቆና፣ አፈናና አድልዎ ዳግም ላይመለስ መቀበሩን በድጋሚ የሚያረጋግጡበት፣ የድህነትና ኋላቀርነት ዘመን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲያበቃ በልማት ጐዳና ላይ እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚያደርጉት ጉዞ ተጠናክሮ መቀጠሉን የሚያበስሩበት፣ ለዚህ ሁሉ ድልና ስኬት ዋነኛውን መሠረት የጣለው የሕገ መንግሥታችን የበላይነት ተከብሮ እንዲኖር

እንደወትሮው ሁሉ በጽናት ዘብ እንደሚቆሙ ቃላቸውን የሚያድሱበት ቀን ነው፡፡ የዘንድሮው በዓል በተለየ ሁኔታ በተለያዩ ዝግጅቶች የሚከበር ሲሆን የተለያዩ ሲምፖዚየሞችና ኮንፈረንሶች የበዓሉ ዋነኛ ገጽታዎች ይሆናሉ፡፡

ይህ ጽሑፍ የዘንድሮው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በሚከበርበት ወቅት ለሀገር አቀፍ ኮንፈረንሶች ለውይይት መነሻ እንዲሆን ታስቦ የተዘገጀ ነው፡፡ ጽሑፉ በዋነኛነት በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ዓላማዎች፣ እምነቶች፣ መሠረታዊ መርሆዎች እና የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ልዩ ባሕሪያት ላይ ያተኩራል፡፡ ጽሁፉ በይዘቱ ሁሉን ነገር የያዘና ተሟላ እንዲሆን በየደረጃው በሚካሄዱ ውይይቶች የሚዳብር መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

የሰነዱ አደረጃጀትም የመጀመሪያው ክፍል መግቢያ ሲሆን በሁለተኛው ክፍል የኢትዮጵያን ሕገ መንግሥት ታሪክ በአጭሩ ይዳሰሳል፡፡ ክፍል ሶስት የሽግግሩ ወቅት ቻርተርና የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት መጽደቅን በተመለከተ የነበረውን ሂደት የሚቃኝ ክፍል ነው፡፡ በክፍል አራት የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ዓላማዎች፣ እምነቶችና መሠረታዊ መርሆዎች በዝርዝር ቀርቧል፡፡ እንደሚታወቀው በዘመናችን ሰዎች ስለሚኖሩበት ሀገር ወይም ስለ ሌላው ሀገር ሕገ መንግሥት በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ሲገልፁ፣ ሲከራከሩና ሲወያዩ መስማት ወይም ማየት እንግዳ ነገር አይደለም፡፡ ሕገ መንግሥት በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ ከዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፣ ከመልካም አስተዳዳር፣ ከምጣኔ ሀብት እድገት ወይም ማሽቆልቆል፣ ከሰብዓዊ መብቶች አያያዝና ጥበቃ ጋር ተያይዞ የዘመናችን መነጋገሪያ አጀንዳ በመሆኑ ሕገ መንግሥታችን የያዛቸው ዓላማዎችና መርሆዎች በዚህ ክፍል በአጭሩ ተዳስሰዋል፡፡

በመጨረሻም የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ልዩ ባሕሪያት የሚብራሩ ሲሆን በተለይም የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ልዩ ባሕሪያትና ለፌዴራሊዝም ሥርዓቱ ምሰሶ ናቸው የምንላቸውን ጉዳዮች በዝርዝር እናያለን፡፡ ክፍል ስድስት የሰነዱ ማጠቃለያ ይሆናል፡፡

*ማስታወሻ

*ይህ የመወያያ ጽሑፍ የሕገ መንግሥቱን መሠረታዊ መርሆዎችና የፌዴራል ሥርዓታችንን መገለጫዎች በማብራራት ለውይይት መነሻ እንዲሆን ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን በሕገ መንግሥቱና ሕገ መንግሥቱን መሠረት በማድረግ በተዘረጋው ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ ሥርዓት በየዘርፉ የተገኙ ውጤቶችና ድሎች በሌሎች ጽሑፎች የተዳሰሱና ወደፊትም በስፋት በየዘርፉ የተገኙ ውጤቶችና ድሎች የዚህ ጽሑፍ አካል የሚደረግ መሆኑን ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡*

## ክፍል ሁለት
## የኢትዮጵያ የሕገ መንግሥት ታሪክ አጭር ዳሰሳ

ሕገ መንግሥት የአንድ ሀገር መንግሥት ዋና መተዳደሪያ ሕግ ነው፡፡ ሕገ መንግሥት በአንድ ሀገር ስለሚኖረው የፖለቲካ ሥርዓት፣ የሥልጣን ባለቤትነት፣ የመንግሥት አካላት አወቃቀር፣ የሥልጣን ክፍፍልና አሰራርን እንዲሁም የዜጐችን መብቶች፣ ነፃነቶች፣ በመንግሥትና በዜጐች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚደነግግ ዋና የፖለቲካና የሕግ ሰነድ ነው፡፡

ሕገ መንግሥት በአንድ ሀገር ውስጥ የበላይ ሕግ ነው፡፡ ምክንያቱም በሀገሪቱ የሚገኙ ልዩ ልዩ ሕጐችና ደንቦች ሁሉ መነሻ መሠረት በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም የአንድ ሀገር ሕገ መንግሥት የሀገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኀበራዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ የሚመሩበት መሠረታዊ ሰነድ ነው፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያ ከ1923 ዓ.ም. ጀምሮ የተለያዩ ይዘቶች ያሏቸው የተጻፉ ሕግጋተ መንግሥት በሥራ ላይ ውለዋል፡፡ ሕግጋተ መንግሥቶቹም የየሥርዓቱን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ባሕሪይን የሚያመለክቱ ነበሩ፡፡ እነዚህም ሕግጋተ መንግሥት በ1923 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ ሥራ ላይ የዋለው ሕገ መንግሥት፣ በ1948 ዓ.ም. የተሻሻለው ሕገ መንግሥት፣ በ1980 ዓ.ም. በወታደራዊው መንግሥት ሥራ ላይ የዋለው ሕገ መንግሥትና ሀገሪቱ ወደ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሽግግር ካደረገች በኋላ በ1987 ዓ.ም. ሥራ ላይ እንዲውል የተደረገው ሕግ መንግሥት ናቸው፡፡

## 1. የ 1923 ዓ.ም. የተፃፈ ሕገ መንግሥት፣

ከብዙ □ታሪክ ጽሑፎችና ሰነዶች ለመገንዘብ እንደሚቻለው ኢትዮጵ□ በፐለም ከሚገኙ ሀገሮች ረዥም፣ ያልተቋረጠና የራሷን ነፃነት ጠብቃ የኖረች ሀገር ናት:: በተለ□ም ባለንበት በአፍሪካ አህጉር ከሚገኙ ሀገሮች ስናስተ□ይ አብዛኞቹ የአፍሪካ ሀገሮች ከአውሮፓ በመጡ ቅኝ ገዢ ወራሪዎች እፀ ሲ□ኑ ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ 1896 ዓ.ም. አድዋ ላይ ባሳየችው ታላቅ ተ□□ሎ የራሷን ነፃነት መጠበቅ ብቻ ሣይሆን በሌሎች ነፃ ያልወጡ ሕዝቦች የነፃነት ተጋድሎ ተምሳሌትና ራዕይ ሆናለች::

ከ1923 ዓ.ም. በፊትም በሀገራችን ኢትዮጵያ እንደ ሕገ መንግሥት ሲያገለግሉ የነበሩ የተለያዩ ሰነዶች ነበሩ:: ሰነዶቹም ፍትሓ ነገሥት፣ ክብረ ነግሥትና ሥርዓተ መንግሥት በመባል የሚታወቁ ናቸው:: እነዚህ ሰነዶች በዋንኛነት ሃይማኖታዊ ይዘት የነበራቸው ሲሆኑ፣ የነገሥታቱን ፍፁማዊነት ከማረጋገጥ ባሻገር የሕዝቡን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጥቅም ከማረጋገጥ አኳያ ብዙም ፋይዳ አልነበራቸውም::

በ1923 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ በተዘጋጀው ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ የተቀመጠው መግለጫ ሕገ መንግሥቱ የዜጎች ይሁንታ ሳያስፈልገው ንጉሡ በፈቃዳቸው ለሕዝቡ የሰጡት ሕገ መንግሥት መሆኑን የሚገልጽ ነበር:: ይህም ሀሳብ በሕገ መንግሥቱ መግቢያ ላይ እንደሚከተለው ሰፍሯል:-

> *" ... እኛ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፣ በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በሕዝብ ኅብረት ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነት ተመርጠን ዘውዱንና ዙፋኑን በሕግ አግባብ ተቀብለን ስንቀባ ለዚህ ታማኝ ለመሆን ለመረጠን ፈጣሪያችን የምንመልሰው ወሮታ፣ የተቀበልነውን*

*አደራ እኛም ሠርተን፣ ጠብቀን ተከታዮቻችንም በሕግ እንዲቀበለንና በደንብ እንዲሠራ ለሀገራችንም በመልካም አስተዳደር በሕግ የሚጠበቅበትን ደንብ ከማቆም በቀር ሌላ የምንመልሰው ወሮታ ስለሌለን ለኢትዮጵያ ልማት ለመንግሥታችን ጽናት ለምንወደው ሕዝባችንም ጥቅምና ሀብት ሆኖ ደስ እንዲያሰኝ ተስፋ ስላደረግን አሳባችንን ገልጠንና አስረድተን የመንግሥት ሕግ እንዲቆም ቀረጥን.... " ይላል፡፡*

ከዚህ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው ንጉሠ ነገሥቱ በእግዚአብሔር እንደተመረጡና እሳቸውም በፍቃዳቸው ሕገ መንግሥቱን ለሕዝቡ እንደሰጡ ነው፡፡ ይህም ንጉሠ ነገሥቱ ለሕዝቡ ተጠያቂነት ያልነበራቸው መሆኑን ከማመልከት ባሻገር፣ ሕገ መንግሥትም የመሪ በጎ ፍቃድ ውጤት ነው የሚል መልዕክት እንደ ነበረው የሚያመለክት ነው፡፡ ስለሆነም የ1923 ዓ.ም. ሕገ መንግሥት በኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጐት ላይ ተመስርቶ ያልተዘጋጀ መሆኑን መረዳት አያዳግትም፡፡ የሥልጣን ባለቤትነት ለንጉሡና ለንጉሣውያን ቤተሰቦች ብቻ የተሰጠ መሆኑንም የ1923ቱ ሕገ መንግሥት በምዕራፍ አንድ ላይ እንደሚከተለው አስፍሮት ይገኛል፡፡

*" ... የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነት ከእየሩሳሌም ንጉሥ ከሰሎሞንና ንግሥተ ሳባ ከተባለችው ከኢትዮጵያ ንግሥት ከተወለደው ቀዳማዊ ምኒልክ ነገድ ተያይዞ ከመጣው ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘር ከተወለደው ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ትውልድ እንደማይወጣ ... "*

በሕገ መንግሥቱ ላይ ተደንግጓል፡፡ ይህም አገላለጽ የሥልጣን ምንጭ ሕዝቡ ሳይሆን መለኮታዊ ባሕሪ መሆኑንና የሥልጣኑም ባለቤት ንጉሡና የንጉሣውያን የዘር ሐረግ ያላቸው ብቻ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ በሀገሪቱ ግዛት ውስዓ የሚገኝ መሬትም ሆነ ሌላ ሀብት፣ እንዲሁም ሕዝቡ የንጉሱ ሀብት እንደሆኑና እርሳቸውም □እግዚአብሔር ተወካ□ እንደሆኑ ይታመን ነበር፡፡

## 2. የተሻሻለው የ1948 ዓ.ም. ሕገ መንግሥት፣

የ1923 ዓ.ም. ሕገ መንግሥት በ1948 ዓ.ም እንዲሻሻል ግፊት ያደረጉት ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች ስለነበሩ □1923 ፐ.ም. ሕገ መንግሥት በተለያዩ ምክንያቶች አማካይነት በየጊዜው ከነበሩ ለውጦች ጋር አብሮ ሊሄድ ባለመቻሉ ማሻሻል የግድ ይል ነበር፡፡ በወቅቱ ለሕገ መንግሥቱ መሻሻል ዋነኛ ምክንያት ሆነው የተወሰዱት ከዚህ የሚከተሉት ነበሩ፡፡

- ኢት□□□ □ተባበሩት መንግሥታት አባል መሆን፣
- በወቅቱ ዘመናዊነት የነበረው ሕ□ መንግሥት ከነበራት ኤርትራ ጋር በ□ዴሬሽን መዋሀድ፣
- በ1923ቱ ሕገ መንግሥት ሊካተቱ ያልቻሉ የምዕራባዊያን አስተሳሰብና ቅስቀሳ፣

እነዚህን ለማስተናገድ ከመሞከር ባሻገር ቀደም ሲል ከነበረው ሕገ መንግሥት መሠረታዊ ለውጥ ነበረው ማለት አይቻልም፡፡ በ1948 ዓ.ም. በተሻሻለው ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ እንደሚከተለው ሰፍሯል:-

*“ … ከሃያ አራት ዓመት በፊት የንጉሠ ነገሥትነታችን ዘመን ሲጀመር <u>በራሳችን ፈቃድ</u> ለታማኙ ሕዝባችን ሕገ መንግሥት ሰጥተን በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግዛት መቋቋሙን አውጀን ስለነበረ፣ የደግ ነገር ሁሉ መገኛ*

*ከሆነ፣ ሁሉን ከሚችል ከእግዚአብሔር በተሰጠን ጥንካሬና ብርታት በዘመነ መንግሥታችን በተነሣው እጅግ ከፍ ባለው የፈተናና የመከራ ጊዜ የተወደደውን ሕዝባችንን መርተን አሰልፈን በሥልጣኔ ደረጃ ተደርሶበት የማይታወቅ እርምጃ ወደ ተገኘበት ዘመን ስላደረስነው፣ የተደረሰበትንም ደረጃ ለማጠንከርና ያገኑን ፀጥታ ለማደላደል ለወደፊቱም እርምጃና ለመጪው ትውልድ ደስታና ደኅንነት ጠንካራ መሠረትን ለመመስረት በንጉሠ ነገሥት መንግሥታችን በረጅሙ ታስቦበትና ባያሌው ተጠንቶ የተሻሻለ ሕገ መንግሥት ስላዘጋጀን፣ ... በዘመነ መንግሥታችን በሃያ አምስተኛው ዓመት በዘውድ በዓላችን መታሰቢያ ቀን ዛሬ ጥቅምት ሃያ አራት ቀን አሥራ ዘጠኝ መቶ አርባ ስምንት ዓመተ ምሕረት በመናገሻ ከተማችን ተሰጠ፡፡ ”*

ከዚህ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው ተሻሽሎ የተዘጋጀውም ሕገ መንግሥት እንደቀድሞው የ1923 ዓ.ም. ሕገ መንግሥት ሕዝቦች ተስማምተውበት ያፀደቁት ካለመሆኑም ባሻገር፣ የዘውዳዊውን መንግሥት ሥልጣንና ተግባር የበለጠ ግልፅ በሆነ መንገድ ያጠናከረና የፖለቲካ ሥልጣኑም ከንጉሡ ቤተሰብ ሊወጣ እንደማይችል ሕገ መንግሥታዊ ከለላ የተሰጠበት ነበር፡፡ ልክ እንደመጀመሪያው ሕገ መንግሥት ንጉሠ ነገሥቱ በሥልጣን የቆዩበትን ሀያ አምስተኛ ዓመት የብር ኢዮቤልዩ በዓላቸውን ሲያከብሩ ከንጉሡ ለተገኘው ሕዝብ የተሰጠ ስጦታ እንጂ ሥልጣን የሕዝብ መሆኑ ታውቆ ሕዝቡ ካለው ሥልጣን ቆርሶ ለንጉሡ የሰጠበት ሰነድ አልነበረም፡፡

በ1923 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ የነበረው ሕገ መንገሥት ከሃያ አምስት ዓመታት በኋላ በ1948 ዓ.ም. እንዲሻሻል ቢደረግም የሥልጣን ምንጭና ባለቤትነትን በተመለከተ ያደረገው መሻሻል አልነበረም፡፡ የንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን ቀደምት እንደነበረው እግዚአብሔር መርጦ ሕዝቡን እንዲገዙ የሾማቸው መሆናቸውን የበለጠ ያጠናከረና የዘውድ አወራረሱም በዝርዝር የንጉሡን የዘር ሐረግ ተከትሎ እንዲብራራ ነበር የተደረገው፡፡

በዘውዳዊው የፖለቲካ ሥርዓት በ1923 ዓ.ም. ሆነ በ1948 ዓ.ም. በተሻሻለው ሕገ መንግሥት ሶስቱ የመንግሥት አካላት ማለትም የሕግ አውጪው፣ የሕግ አስፈፃሚውና የሕግ ተርጓሚው ተግባርና ኃላፊነቶች በግልፅ በሁለቱም ሕግጋተ መንግሥት ያልተቀመጡና ሆኖም ስልጣን በሙሉ በንጉሡ እጅ እንደነበረ የሕግጋተ መንግሥቱ ይዘቶች ያመለክታሉ፡፡ በ1923 ዓ.ም. ሆነ በ1948 ዓ.ም. ሕግጋተ መንግሥት መሠረት ሁለት ምክር ቤት ያለው ፓርላማ እንዲመሠረት ቢደረግም ፓርላማው የሚያወጣውን ሕግ ንጉሠ ነገሥቱ ካልተቀበሉት ሕግ ሆኖ ሊፀድቅና ሊሠራበት አይችልም ነበር፡፡

የዳኝነት ሥራን በተመለከተም በሁለቱም ሕግጋተ መንግሥት የተገለፀ ነገር ቢኖርም ዳኞች ፍርድ ይሰጡ የነበሩት በንጉሠ ነገሥቱ ሥም ሲሆን፣ ከዚህም ባሻገር ንጉሠ ነገሥቱ በቀጥታ ፍርድ የሚሰጡበትና የመጨረሻው ይግባኝ ሰሚ የሆነ ፍትህ አካል "የዙፋን ችሎት" በሚል የሚታወቅ ተቋም የነበረ በመሆኑ ንጉሠ ነገሥቱ የዳኝነቱንም ተግባራት ያከናውኑ ነበር ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ንጉሠ ነገሥቱ የርዕሰ ብሔርነቱን አስተዳደር (Government) እና የዳኝነቱን ሥልጣን ጠቅልለው መያዝ ችለዋል፡፡ ይህም በሀገሪቱ የዘውዳዊ ሥርዓት ፈላጭ ቆራጭነት እንዲሰፍን ያደረገ መሠረታዊ ጉዳይ መሆኑን መረዳት አያዳግትም፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ በ1923 ዓ.ም. የፀደቀው ሕገ መንግሥትም ሆነ በ1948 ዓ.ም. የተሻሻለው ሕገ መንግሥት ሕዝቡ ያልመከረበት፣ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መሠረታዊ የሉዓላዊነት ጥያቄ መልስ ያላገኘበት፣ የንጉሡ ነገሥቱን ስልጣን ሕጋዊ ለማድረግና ለማጠናከር የንጉሥን ፈቃድ እና ፍላጐት ማዕከል አድርገው የተቀረጹና የፀደቁ መሆናቸው የሚያከራክር አይደለም፡፡ አምባገነናዊ የሆነውን የዘውዳዊ እና ፊውዳላዊ ሥልጣኑን ሕጋዊ ለማድረግና የንጉሡን ስልጣን በሚያጠናከር መንገድ ለመጠቀም፣ የሕዝቡን የሉዓላዊነትና የስልጣን ባለቤትነት ጥያቄን ለመጨፍለቅ በሚያመች መንገድ ሕገ መንግሥቱን ለመጠቀም በመሞከራቸው የሕዝቡን አመጽ የበለጠ በማቀጣጠል ንጉሡንም ሆነ ያፀደቁትን ሕገ መንግሥት መቀመቅ እንዲወረዳቸው የሚያስገነዝበን ነው፡፡

3. የ1980 ዓ.ም. የደርግ ሕገ መንግሥት፣

በኢትዮጵያ የንጉሣዊው አገዛዝ የዘለቀው እስከ 1966 ዓ.ም. ድረስ ሲሆን አገዛዙ ሊወድቅ የቻለው በዚያን ዓመት በተቀጣጠለው አብዮት ምክንያት ነበር:: ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ተግባራዊ ማድረግ በመከልከሉ በ□ቦታው □ተቃውሞ እንቅስቃሴዎች መስፋፋት ጀመሩ:: በቀድሞው አጠራር □□ጸም፣ የትግራይ፣ □ባሌ፣ የአሩሲ፣ □ሲ□ሞ እና የከፋ ገበሬዎች አመጽ ለዚህ በቂ ምሳሌ ሊሆን ይችላል:: እነዚህ እንቅስቃሴዎች ብ□ ሕይወትን የቀጠፉ ቢሆንም የተደራጀና የተጠናከረ አመራር ያልነበራቸው በመሆኑ የታለመላቸውን ግብ ሊመቱ አልቻሉም ነበር::

□ተቃውሞ እንቅስቃሴው በ□ቅቱ እስከነበሩት ባለሥልጣናት ድረስ በመዝለቅ አገዛዙን ለመጣል በ1953 ዓ.ም. መፈንቅለ መንግሥትን እስከመሞከር ደርሶ የነበረ

ቢሆንም መጨረሻው ይህንን መፈንቅለ መንግሥት ያቀነባበሩ ባለሥልጣናት በሞት መቀጣትን አስከትሎ ነበር፡፡ የተቃውሞ እንቅስቃሴው በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ዘንድ በመቀጣጠል ተማሪዎቹ በተለያዩ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ውስዓ እንዲገቡ አድርጎ ነበር፡፡ ከ1957 ዓ.ም. ጀምሮ የተማሪዎች እንቅስቃሴ በወቅቱ የነበረውን የመሬት ስሪት በመቃወም «መሬት ላራሹ» □ሚለውን መፈክር በማንገብ መሬት ከመሬት ከበርቴዎች ተነጥቆ ለአርሶ አደሮች እንዲከፋፈል በመጠየቅ ቀጥሎ ነበር፡፡

□ካቲት 1966 ዓ.ም. ገበሬዎች፣ ተማሪዎች፣ መምሕራን፣ □ታክሲ ሾፌሮችና ሌሎችም በአንድ ላይ ግብታዊ የሆነ የአብዮት እንቅስቃሴ አደረጉ፡፡ በወቅቱ የተደራጀና የተዘጋጀ አብዮቱን ወደተፈለገበት አቅጣጫ ሊመራ የሚችል የፖለቲካ ፓርቲ አልነበረም፡፡ በአብዮቱ እንቅስቃሴ የንጉሣዊው አገዛዝ መረብ ሊበ□ጠስ የቻለ ቢሆንም ሀ□ሪቱ በ□ታደራዊ አገዛዝ ሥር ልትወድቅ ቻለች፡፡ □□□ዊ □ታ□ራዊ አስተዳደር ደርግ የሥልጣን ክፍተቱን በመጠቀም «ኢትዮጵያ ትቅደም» □ሚለውን መፈክር በማንገብ ሀገሪቱን ወደባሰ ብጥብጥና ትርምስ መምራት ጀመረ፡፡ የደርግ አስተዳደር ሥልጣኑን ለሕዝቡ ለመስጠትም ሆነ የፖለቲካ ሥልጣኑን ከወታ□ራዊ ክፍሎች ውጭ ከሲቪሎች ጋር ለመጋራት ፈቃደኛ ያልነበረ ከመሆኑም በላይ ሀሳብን □መፅለ□፣ ሠላማዊ ሠል□ □ማ□ረፅ፣ የመደራጀትና ሌሎችም የዲሞክራሲ መብቶችን በይፋ የከለከለበት ሁኔታ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት የወታደራዊው አምባገነናዊ መንግሥት የመብት ጥያቄ ይዘው የተነሱ ዜጐችን ቀይ ሽብር በሚል ያለፍርድ የበርካቶችን ሕይወት የጨፈጨፈበት እንዲሁም የዘር ማጥፋት ዘመቻ የተካሄደበት ነበር፡፡

የሕዝብን የመሬት ጥያቄ በተመለከተ የተለያዩ አዋጆችን ያወጣ ሲሆን በዋናነት የሚጠቀሱት በ1967 ዓ.ም. የወጡት ሁለት አዋጆች ናቸው:: ከነዚህም ውስጥ አንዱና ዋነኛው ተ□ቃሽ አዋጅ ቁጥር 31/1967 ዓ.ም. ሲሆን ይህ አዋጅ የወጣው □□□ር መሬትን የሕዝብ ንብረት ለማድረግ ነበር:: በዚህ አዋጅ መሠረት አዋጁ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ሁሉም የገጠር መሬት የኢትዮ□□ ሕዝቦች የጋራ ሀብት እንደሆነ የሚደነግግ ቢሆንም አርሶ አደሩ በመሬቱና በሚያመርተው ምርት ተጠቃሚ አልሆነም::

ሌላው ተጠቃሽ አዋጅ ቁዓር 47/1967 ዓ.ም. ሲሆን ይህ አዋጅ የሚደነግገው □ከተማ መሬትና ትርፍ ቤት አዋጁ ተግባራዊ ከሆነበት ቀን ጀምሮ የመንግሥት ሀብት እንደሆነ ነው:: በአዋጁ መሠረት አንድ ሰው □ይም ቤተሰብ ከአንድ በላይ የከተማ ቤት ሊኖረው አይገባም:: በእነዚህና በሌሎችም አዋጆች የደርግ አስተዳደር የከተማና የገጠር መሬትን፣ ትርፍ ቤቶችን፣ የግል ትምህርት ቤቶችን፣ □ብሪካዎችን፣ እርሻዎችን ወዘተ... በመውረስ የግል ሀብት እድገትን ሊገታ ችሏል::

ወታደራዊው መንግሥትም ሥልጣን ላይ በወጣ በአሥራ ሦስት አመቱ በ1980 ዓ.ም. ሕገ መንግሥት እንዲዘጋጅና ተግባራዊ እንዲሆን አደረገ:: የዚህ ሕገ መንግሥት ዝግጅት ለይስሙላ ካልሆነ በስተቀር የተሟላ የሕዝብ ተሳትፎ ያልነበረበት ሲሆን፤ ከሥርዓቱ አምባገነናዊነት በመነጨም ሕዝቡ በልበ ሙሉነት ይህ በሕገ መንግሥቱ እንዲካተት እፈልጋለሁ ይህን ደግሞ አልፈልግም እንዲል የሚያስችለው ሁኔታ አልነበረም:: ስለሆነም ሕገ መንግሥቱ ያለሕዝብ ወሳኝ ተሳትፎ በብልጣ ብልጥነት ተረቅቆ እንዲፀድቅ የተደረገ ነበር::

በዚህ ሕገ መንግሥት "ሥልጣን የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ነው" ተብሎ የተገለፀ ቢሆንም ይህ ለይስሙላ ካልሆነ በስተቀር ሠርቶ አደሩ ሕዝብ የሥልጣን ምንጭም ሆነ የሥልጣን ባለቤት ያልነበረ መሆኑን ከነበረው ሁኔታ መረዳት ይቻላል፡፡ ሕገ መንግሥቱን በማዘጋጀትና በማጽደቅ ሂደት የሕዝቡ ተሳትፎ አናሳና ለይምሰል የነበረ ሲሆን፣ የወታደራዊው መንግሥት ዓላማም በሶሻሊስት ርዕዮት ሽፋን የፖለቲካ ሥልጣኑን በሙሉ አማክሎ መያዝ ስለነበረ የሀገሪቱ ዜጎች የሥልጣን ባለቤት እንደሆኑ የሚያመለከት ምንም ነገር አልነበረም፡፡ የሥልጣን ምንጭነትን በተመለከተ በሁለቱ የአገዛዝ ሥርዓት በነበሩት ሕግጋተ መንግሥት መካከል የነበረው መሠረታዊ ልዩነት የዘውዳዊው ሕገ መንግሥት ዘውዳዊ ሲሆን፣ የወታደራዊው ደግሞ ስመ-ሶሻሊስታዊ መሆኑ ብቻ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህም የኢትዮጵያ ሕዝብ ለይስሙላ ካልሆነ እንደራሴዎቹን ለፓርላማው /ለብሔራዊ ሸንጎ/ የመጠቆምም ሆነ የመምረጥ ሕገ መንግሥታዊ መብት እንዳልነበረውና ዕጩዎችን ለብሔራዊ ሸንጎ የሚያቀርበው ራሱ ፓርቲው ከመሆኑም በላይ የወታደራዊው መንግሥት የሥልጣን ምንጭ የጦር መሳሪያው ብሎም በስመ ኮሚኒስት ርዕዮተ ዓለም አቀናባሪነት ዓላማውን ለማራመድ ይጠቅመኛል በሚል ያቋቋማቸው አካላት ነበሩ፡፡

በአጠቃላይ የወታደራዊው መንግሥት ሕገ መንግሥት ሕዝቡ በሚገባ ያልተሳተፈበት፣ በይዘቱም ብዙ ችግሮች የነበሩበት፣ ፕሬዚዳንቱ ሕግ አውጪውን፣ ሕግ አስፈፃሚውንና ፍርድ ቤቶችን ጨምሮ የመቆጣጠር ስልጣን የነበረው መሆኑ፣ በሕግ የበላይነት የማያምን በመሆኑ ሕገ መንግሥቱ የሕዝብ ፍላጐት መገለጫ መሆኑን ያላገናዘበ ነው ማለት ይቻላል፡፡

# ክፍል ሦስት
# የሽግግሩ ወቅት ቻርተርና የኢ.ፌ.ዴ.ሪ.
# ሕገ መንግሥት መጽደቅ

በንጉሱ ዘመነ መንግሥትም ሆነ በወታደራዊው አገዛዝ ሥራ ላይ ውለው የነበሩት ሕግጋተ መንግሥት የኢትዮጵያን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሉዓላዊነትና የሕዝቡን መሠረታዊ ጥያቄ ለመፍታት ባለመቻላቸው አምባገነናዊ ፈላጭ ቆራጭ የነበረውን ዘውዳዊ አገዛዝ ለማስወገድ ከዚያም በኋላ የሕዝቡን የነፃነትና የዲሞክራሲ ትግል በአቋራጭ በመንጠቅ ወታደራዊ አምባገነናዊ አስተዳደር የመሠረተውን ደርግ ለመገርሰስ በተካሄደው ተጋድሎ በሀገሪቱ ከፍተኛ የሆነ ሰብዓዊ እልቂት አድርሷል፣ ከፍተኛ ግምት ያለው ቁሳዊ ሀብት ወድሟል፡፡ ኢኮኖሚያዊ ዕድገቷም ተንኮታኩቶ ሕዝቦቿ ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩባት፣ በምግብ ራሳቸውን መቻል አቅቷቸው በረሃብ ያለቁበትና ለስደትና ለልመና የተዳረጉበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡

የደርግ መንግሥት ማንኛውንም ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄ በኃይልና በጉልበት ለመፍታት ያደረገው ሙከራ ከፍተኛ የሆነ ሰብዓዊና የቁሳዊ ሀብት እልቂትና ውድመት ከማስከተሉ በስተቀር መሠረታዊ የሆነውን የሕዝቡን የሉዓላዊነትና የመብት ጥያቄ ለማዳፈን ባለመቻሉ የተጀመረው የትጥቅ ትግል ተጠናክሮ በኢህአዴግ አሸናፊነት ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም. የደርግ መንግሥት ተገረስሶ ሕልውናው አክትሟል፡፡

የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር ከመጽደቁ በፊት የደርግ ሥርዓት በመገርሰሱ የሚነሱ ጥያቄዎች ነበሩ። ከእነዚህም ዋነኛ ጥያቄዎች መካከል የመንግሥት አስተዳደር እንዴት ይዋቀራል እና ሕገ መንግሥት እንዴት ይረቀቃል

የሚሉት ነበሩ። ለእነዚህና ሌሎች በወቅቱ አንገብጋቢ ለነበሩ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት እንዲያስችል በሀገሪቱ በወቅቱ የነበሩ ፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲሰባሰቡ ተ□ብ□ዋል። በዚህም መሠረት □ሰላምና የዴሞክራሲ ኮንፈረንስ በማካሄ□ □ሀገሪቱን የወደፊት ዕጣ ፈንታ መወሰን እንዲቻል በወቅቱ ወደ 27 የሚደርሱ □□ለቲካ ፓርቲዎች፣ ንቅናቄዎች እንዲሁም ተቋማት ተጋብዘው የተሳተፉ ሲሆን ጥሪውን ባለመቀበል በኮንፍረንሱ ላይ ተሳትፎ ያላደረጉም ነበሩ። ከእነዚህ መካከል የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ (EPRP) ይጠቀሳል።

የኮንፈረንሱ ተሳታፊዎች የሀገሪቱ አስተዳደር እንዴት ይመራ ከሚለው በመነሳት ለ□ዜው ለሽፅፅር □ቅት የሚያገለግል የሽግግር ወቅት ቻርተር አጽድቀዋል። ይህ የሆነው ኢህአዴግ ሀገሪቱን በተቆጣጠረ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ሲሆን □ህ ቻርተር በሽፅፅሩ ወቅት ከሁሉም ሕጎች የበላይ ሆኖ እንዲያገለግል ስምምነት ላይ ተደረሰ፡፡ በኮንፈረንሱ ላይ የነበረው ስምምነትና የውይይት መንፈስ ከዚያ በፊት ታይቶ በማ□ታወቅ ሁኔታ በሀ□ሪቱ ውስጥ የብዙ ፓርቲዎች የጋራ አስተዳደር በሽግግር እንዲፈጠር መንገድ የከፈተ ነበር።

የሽፅፅሩ □ቅት ቻርተር የሚከተሉት ዋና ዋና ዓላማዎች ነበሩት፡-

- ከዚያ በፊት የነበረው የጭቆናና የብዝበዛ ሥርዓት እንዲያከትም ማድረግ፣
- የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሀገሪቱን የሚገነቡበትንና ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር □ሚ□ዓሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- □ሁሉም ሕዝቦች እኩልነት፣ ነፃነት እና የራስን ዕድል በራስ መወሰን ዋነኛ መርህ የሚሆንበትን አዲስ ምዕራፍ መክፈት፣
- መቆራቆስ የሌለበት መልካም ጉርብትናን መፍጠር፣

• ለሕዝብ ተጠሪ የሆነ በምርጫ የሚቋቋም አስተዳደር መፍጠር ነበሩ፡፡

በቻርተሩ አንቀጽ 10 እና 11 ተደንግጎ የሚገኘውና በዚህ ክፍል ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ የሽግግሩ ወቅት □ተ□ካዮች ምክር ቤት ሕገ መንግሥት አርቅቆ የሚያዘጋጅ አካል ማለትም የሕገ መንግሥት ኮሚሽን እንደሚቋቋም፣ □ተረቀቀው ሕ□ መንግሥት በሽግግር መንግሥት በተ□ካዮች ምክር ቤት ሲፀ□ቅ ለሀ□ሪቱ ሕዝቦች ለውይይት እንደሚቀርብ፣ ከሕ□ብ ውይይት በኋላ የመጨረሻው ረቂቅ የሕ□ መንግሥት ጉባዔ ተብሎ የሚቋቋመው አካል እንዲያፀድቀው የሚቀርብ መሆኑ፣ □ሕገ መንግሥት ጉባዔ ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የተመረጡ ተ□ካዮች የሚኖሩበት ሆኖ ብቸኛ ተፅባሩ ሕገ መንግሥቱ ላይ ተወያይቶ ማጽደቅ ብቻ እንደነበር ከላይ በተገለጹት የቻርተሩ ድንጋጌዎች ተገልጿል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አምባገነናዊ ሥርዓትን በማስወገድ የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው ለመወሰንና ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና ልማት ለማሸጋገር በድልድይነት ያገለገለና ከቀደምት ሕግጋት መንግሥት በቅርፁ፣ በይዘቱና በአተገባበሩ መሠረታዊ ልዩነት የነበረው ሰነድ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ቻርተሩ ለዘመናት መልስ ያላገኘውን የሕዝቦች ሉዓላዊነትና የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል ማለትም የእያንዳንዱን ብሔር ብሔረሰብና ሕዝብ፣

• የራሱን ማንነት የመጠበቅ፣ የማስከበር፣ ባሕሉንና ታሪኩን ለማበልፀግ እንዲሁም በማዕከላዊ መንግሥት ውስጥ በነፃና አድሎ በሌለበት ሁኔታ የመወከል፣

- ከላይ የተጠቀሱት መብቶች ታገዱ፣ ተረገጡ ወይም ተሸራረፉ ብሎ በሚያምንበት ጊዜ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ድረስ የማረጋገጥ መብት እንዳለው በግልጽ የደነገገ የመጀመሪያው ሰነድ ነው፡፡

ቻርተሩ ለአጭር ጊዜ ሀገሪቱ የምትመራበትና መንግሥት የሚተዳደርበት የሕግ ሰነድ እንጂ ለዘላቂነት እንዲያገለግል ታስቦ የፀደቀ ሕገ መንግሥት ባለመሆኑ በሽግግር ወቅት ለነበረው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን የማቋቋም ግዴታ እንደጣለበት በአንቀጽ 9/ሰ/ ደንግጓል፡፡

በዚህ መሠረት የሽግግር ወቅት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በቻርተሩ የተጣለበትን ሕዝባዊ አደራና ኃላፊነት ለመወጣት በነሐሴ ወር 1984 ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 24/1984 የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ በማወጅ የሕገ መንግሥት አርቃቂ ከሚሽን አቋቁሟል፡፡ አርቃቂ ከሚሽኑ በተሰጠው ስልጣንና ሃላፊነት መሠረት ግዴታውን ለመወጣት በትጋት ሰርቷል፡፡

ኮሚሽኑ በሽግግሩ ወቅት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰየሙና ተልዕኳቸው፣ ስልጣንና ኃላፊነታቸው በሕግ ተዘርዝሮ የተሰጣቸው ሀያ ዘጠኝ የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን አባላት የነበሩት ሲሆን በኮሚሽኑ ውስጥ የአባላቶች ተዋጽዖን በተመለከተ በአዋጁ አንቀጽ 7 ንኡስ አንቀጽ 2 እንደተመለከተው:-

- ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 7 አባላት
- ከፖለቲካ ድርጅቶች 7 አባላት
- ከሠራተኛ ማኅበራት 3 አባላት
- ከኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት 3 አባላት

- የሕግ ባለሙያ ማኅበር 2 አባላት
- ከኢትዮጵያ መምሕራን ማኅበር 2 አባላት
- ከኢትዮጵያ የጤና ባለሙያዎች ማኅበር 2 አባላት
- ከሴቶች ተወካይ 3 አባላት

ተሳታፊ እንዲሆኑ የተደረገ ሲሆን ስልጣንና ተግባራቸውም:-

- የሽግግር ቻርተሩን መንፈስ ተከትለው ረቂቅ የሕገ መንግሥት ሰነድ የማዘጋጀት፣
- በሕገ መንግሥታዊ መርሆዎች ላይ ትምሕርታዊ ውይይቶችን፣ ሴሚናሮችንና ሲምፖዚየሞችን በማዘጋጀት ኅብረተሰቡን ማወያየት፣
- በረቂቅ ሕገ መንግሥቱ ላይ ኅብረተሰቡን የማወያየት፣
- ረቂቅ ሕገ መንግሥቱን ለሽግግሩ መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመላክ፣
- ረቂቁ በሽግግሩ መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሁንታ ካገኘ በኋላ ለኅብረተሰቡ የማስተዋወቅና የማሰራጨት፣
- በረቂቅ ሕገ መንግሥቱ ላይ ከክልልና ከወረዳ ምክር ቤቶች እንዲሁም ከሌሎች ሴክተሮች የተሰጡ አስተያየቶችን የመቀበል የማሰባሰብና የማደራጀት፣
- ከኅብረሰተቡ ለቀረቡ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ምላሽ የመስጠት፣
- ከሕዝብ የተሰጡ አስተያየቶችን በማካተት የመጨረሻውን ረቂቅ ሕገ መንግሥት ለሽግግሩ መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የማቅረብ፣
- የመጨረሻውን ረቂቅ ሕገ መንግሥት ለሕገ መንግሥት ጉባዔ (Constituent Assembly) ለውሳኔ የማቅረብ፣

የሚሉት ይገኙበታል፡፡ ኮሚሽኑ እነኚህን ተግባራት በሁለት ዋና ዋና ምዕራፎች በመክፈል ሲያከናውናቸው ቆይቷል፡፡ እነኚህም የሲቪክ ትምህርት እና የኮንሰልቴሽን ምዕራፎች ሲሆኑ በዚህም የኅብረተሰቡን ተሳትፎ በማረጋገጥና ኅብረተሰቡም በሕገ መንግሥት ማርቀቅና ማጽደቅ ሂደት ውስጥ የራሱ አስተዋጽዖ እንዲኖረውና ሕገ መንግሥቱ የራሴ ነው የሚል አመለካከት ይዞ እንዲወጣ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

በዚህም መሠረት ኮሚሽኑ የመጀመሪያውን ረቂቅ አዘጋጅቶ የሽግግሩን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስምምነት ካገኘ በኋላ:-

- በሕገ መንግሥታዊ ጽንሰ ሀሳቦችና በረቂቅ ሕገ መንግሥቱ ላይ በተለያዩ የትምሕርት ተቋሞች እና በመንግሥት መገናኛ ዘዴዎች ውይይቶችንና ሲምፖዚየሞችን በማዘጋጀት ረቂቁን ሊያዳብሩ የሚችሉ ሀሳቦችን እና አስተያየቶችን በማሰባሰብ፣
- ረቂቁ በወቅቱ ለተቋቋሙት የክልል መስተዳድር ምክር ቤቶች እና ለወረዳ ምክር ቤት አባላት ቀርቦ እንዲወያዩበት እና አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት በማድረግና ከምክር ቤቶቹ የተሰጠውን አስተያየት በግብአትነት በመጠቀም ፣
- በረቂቅ ሕገ መንግሥቱ ላይ ሕዝቡ በየቀበሌው ውይይት በማድረግ አስተያየት ሊሰጥ የሚችልበት መድረክ በማመቻቸት ሕዝብ በረቂቁ ላይ የሰጠውን ትችትና አስተያየት በማሰባሰብና በግብአትነት በመጠቀም፣
- በተለያየ ጊዜ ረቂቅ ሕገ መንግሥቱን አስመልክቶ ከሕዝብ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ማብራሪያና ገለፃ በመስጠት፣

ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የቀረቡትን አስተያየቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች በማካተት የመጨረሻውን ረቂቅ ሕገ መንግሥት ለተወካዮች ምክር ቤት አቅርቧል፡፡

የመጨረሻው ረቂቅ የቀረበለት የሽግግሩ ወቅት የተወካዮች ምክር ቤት በረቂቁ ላይ ከተወያየና ተገቢ ናቸው የሚላቸውን ተጨማሪና የማሻሻያ ሀሳቦች በመጨመር ረቂቁን በማጽደቅ ለሕገ መንግሥት ጉባዔ እንዲቀርብ ወስኗል፡፡ የሽግግሩ ወቅት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕገ መንግሥቱ አርቃቂ ኮሚሽን ስራን በተመለከተ ከሚያደርገው ክትትል ጐን ለጐን የሕገ መንግሥት ጉባዔ አባላትንና ሌሎች ምርጫዎችን ነፃ፣ ገለልተኛና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ለማከናወን የሚያስችል የኢትዮጵያ ምርጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 64/1985 ዓ.ም. በማውጣት የሕገ መንግሥት ጉባዔ አባላት ምርጫ እንዲከናወን አድርጓል በዚህም ቁጥራቸው 543 የሆነ የሕገ መንግሥት ጉባዔ አባላት ነፃ፣ ቀጥተኛ እና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ እንዲመረጡ ተደርጓል፡፡ የሕገ መንግሥቱ የመጨረሻ ረቂቅ በሕዝብ ድምጽ ለዚሁ ተግባር ለተመረጡት የሕገ መንግሥት ጉባዔ ለውይይት በማቅረብ በሰፊው ከተመከረበት በኋላ ኅዳር 29 ቀን 1987 ዓ.ም. ጸድቋል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት ረቂቅ ዝግጅት ሂደት በሕገ መንግሥት ረቂቅ አሰራር ሂደት ሊከበሩ የሚገባቸውን መሠረታዊ መርሆዎች ተግባራዊ በማድረግ የተከናወነ መሆኑን ከዚህ ሂደት መረዳት ይቻላል፡፡ ሌላው ተግባር የአርቃቂ ኮሚሽኑ አባላት ተዋጽዖ ለሕዝብ ግልጽ የሆነና ስልጣንና ተግባሩም በሕግ የተዘረዘረ መሆኑ፣ በሽግግሩ ወቅት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመጀመሪያ

ደረጃ ተቀባይነት ያገኘው ረቂቅ ለክልሎችና የወረዳ ምክር ቤት አባላትና መላው ሕዝብ ተወያይቶ አስተያየት የተሰጠበት መሆኑን፣ የመጨረሻው ረቂቅ በሽግግሩ ወቅት የተወካዮች ምክር ቤት ታይቶና ፀድቆ ለሕገ መንግሥት ጉባዔ የቀረበ መሆኑን ሂደቱ ግልጽ አሳታፊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሁም ዘመናዊ አስተሳሰብና ጥንቃቄ የተሞላበት የነበረ መሆኑን ያስረዳል፡፡

# ክፍል አራት
# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት ዓላማዎች፣ እምነቶች፣ መሠረታዊ መርሆዎችና ልዩ ባሕሪያት

## 4.1. የሕገ መንግሥቱ ዋና ዋና ዓላማዎችና እምነቶች

የሕገ መንግሥቱን መሠረታዊ መርሆዎችና ልዩ ገጽታዎች ከመግለፃችን በፊት ሕገ መንግሥቱን በነፃ ፈቃዳቸው ያፀደቁት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ይዘው የተነሱትን ዓላማና የጋራ ያደረጓቸውን እምነቶች በመንደርደሪያነት ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው፡፡ የሕገ መንግሥቱ መሠረታዊ ዓላማዎችና እምነቶች ተንፀባርቀውና ግልጽ በሆነ ሁኔታ ተቀምጠው የሚገኙት በሕገ መንግሥቱ መግቢያ ላይ ሲሆን የዓላማዎቹና የእምነቶቹ ባለቤቶች የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ናቸው፡፡ የእምነቶቹና የዓላማዎቹ ባለቤቶች መሆናቸው የሚታወቀውም የሕገ መንግሥቱ መግቢያ የሚጀምረው “ ... *እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ...* ” በሚል ለየት ያለ አገላለጽ በመሆኑ ነው ፡፡

በዚህም መሠረት ሕገ መንግሥቱ ከሌሎች ሕግጋተ መንግሥት የሚለየው የሀገራችንን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሕገ መንግሥቱ ባለቤቶች መሆናቸውን እውቅና በመስጠት የራሳቸው ሕገ መንግሥት እና የሉዓላዊነታቸው መገለጫ ተደርጎ መቀረጹ ነው፡፡

የዓላማዎቹ መነሻና ምክንያት በሀገራችን በነበሩት ስርዓቶች ሕዝቦች ለረጅም ዘመናት የሰላም የዴሞክራሲና የፍትሀዊ ልማትና እድገት ተጠቃሚነት ተነፍጓቸው ስለነበር ይልቁንም የእርስ በእርስ ጦርነት፣ የፀረ ዴሞክራሲ አገዛዝ፣

ብሔራዊ ጭቆና እና ድህነት ሰፍኖ በመቆየቱ ይህን በሚቀይር ሁኔታ ስር ነቀል ለውጥ ማምጣት እና በእኩልነት፣ በነፃ ፈቃድና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ አዲስ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት መገንባት በማስፈለጉ ነው ፡፡

በዚሁ መነሻ ዘላቂ ሰላምና ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ ማስፈንና ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት እንዲፋጠን ማድረግ ዘርዘር ያሉ ዓላማዎች ሲሆኑ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰን መብታቸውን በመጠቀም በነፃ ፍላጎታቸውና ፈቃዳቸው እንዲሁም በሕግ የበላይነት ላይ በመመስረት አንድ የፖለቲካ እና የፖለቲካ ማኅበረሰብ በጋራ መገንባት ዘላቂ ዓላማቸው ሲሆን ለዚህም ዓላማ መሳካት ሕገ መንግሥቱ ቁርጠኛ ፍላጎታቸውን የገለፁበት የሕግና የፖለቲካ ሰነድ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ይህን አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ የመገንባት ዓላማ ለማሳካትና ከግብ ለማድረስ የግለሰብና የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መሠረታዊ መብቶች መከበር፣ የፆታ እኩልነት መረጋገጥ፣ ሃይማኖቶችና ባሕሎች ካለ አንዳች ልዩነት በእኩልነት መራመዳቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሁኔታዎች በመሆናቸው የሕገ መንግሥቱ ባለቤቶች እነዚህን እሴቶች የጽኑ እምነታቸው መገለጫዎች አድርገዋቸዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የየራሳቸው አኩሪ ባሕል፣ አሰፋፈርና መልክዐ-ምድር ያላቸው የነበረ ቢሆንም በተለያዩ የግንኙነት መስኮችና ደረጃዎች በመተሳሰር አብረው የኖሩባትና የሚኖሩባት የጋራ ሀገር ያፈሩት የጋራ ጥቅምና አመለካከት ያላቸውና ከታሪክ የተወረሰውን የተዛባ

ግንኙነት በማረም መጪውን ዕድላቸውን የጋራ ጥቅምን በማሳደግ ላይ መመስረት ያለባቸው መሆኑን በአጠቃላይም አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ የመገንባትን አስፈላጊነት የእምነቶቻቸው መገለጫዎች ያደረጓቸው እና ሕገ መንግስቱም ከላይ ለተገለፁት ዓላማዎቻቸውና እምነቶቻቸው ማሰሪያ ሰነድ አድርገው ያፀደቁት መሆኑን እንረዳለን፡፡

በአጠቃላይ ሕገ መንግሥቱ ትኩረት ያደረገው በሕግ የበላይነት እና በብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ የግለሰብና የቡድን መብቶች በአንድ ላይ የሚከበሩበት፣ በሃይማኖቶችና ባሕሎች መካከል አድሎ የማይደረግበት፣ የፆታ እኩልነት የተረጋገጠበት፣ ዘላቂ ሰላምና ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ የሰፈነበት አንድ የፖለቲካ እና የፖለቲካ ማኅበረሰብ የመገንባት ዓላማ ላይ ነው፡፡

## 4.2. የሕገ መንግሥቱ መሠረታዊ መርሆዎች፣

የሕገ መንግሥቱን መሠረታዊ መርሆዎች የምናገኘው በምዕራፍ ሁለት ከአንቀጽ 8 እስከ 12 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ውስጥ ነው፡፡ እነዚህ መርሆዎች በሀገራችን የዴሞክራሲያዊ መንግሥትና ሥርዓት ግንባታ ሂደት ውስጥ በጣም አስፈላጊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ በመሆናቸው ሌሎች የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች የተመሠረቱባቸውና የሚገዙባቸው መርሆዎች ናቸው፡፡

የሕገ መንግሥቱ መሠረታዊ መርሆዎች ሕገ መንግሥቱ የቆመባቸው ምሰሶዎች ወይም መሠረቶች ሆነው የሚያገለግሉ ሲሆን የበታች ሕጎች ሲወጡ፣ መንግሥት ተግባራቱን ሲያከናውን እነዚህን መርሆዎች ባገናዘበ መልኩ መሆን አለበት፡፡

ሕገ መንግሥቱ በዋናነት በአምስት መሠረታዊ መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ሲሆን እነዚህን መርሆዎች ቀጥሎ በአጭሩ መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡

### 4.2.1. የሕዝብ ሉዓላዊነት

ይህ መርህ ተደንግጎ የምናገኘው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 8 ላይ ሲሆን ድንጋጌውም

1. የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸው፡፡
2. ይህ ሕገ መንግሥት የሉዓላዊነታቸው መግለጫ ነው፡፡
3. ሉዓላዊነታቸውም የሚገለፀው በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት በሚመርጧቸው ተወካዮቻቸውና በቀጥታ በሚያደርጉት ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ አማካይነት ይሆናል፡፡

የሚል ሲሆን ይህም ሶስት ዋና ዋና ሀሳቦችን የያዘ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ሕገ መንግሥቱ ስር ነቀል በሆነ ሁኔታ ያስቀመጠው ነገር በሀገራችን የመንግሥት የሥልጣን ምንጭና ባለቤት እንዲሁም ተጠቃሚ አንድ ሰው ወይም ቡድን ወይም ብሔር/ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሳይሆን ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መሆናቸውን ነው፡፡ ድንጋጌው የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነታቸው ተከብሮ ለራሳቸው ጉዳዮች ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩበት በተለያዩ የመንግሥት የሥልጣን እርከኖች በጋራ ጉዳዮቻቸው ደግሞ ሚዛናዊ ተዋጽዖ ኖሯቸው የሚሳተፉበት ሁኔታ እንዲኖር ምቹ መሠረት የጣለ የሕግ ማዕቀፍ ነው፡፡

በኛ ሕገ መንግሥትና ሀገራዊ ሁኔታ የሕዝብ ሉዓላዊነት የሚገለፀው በሁለት መንገዶች ነው፡፡ የመጀመሪያው ሕዝቦች በሕገ መንግሥቱ መሠረት በቀጥታ በሚመርጧቸው ተወካዮቻቸው አማካኝነት ሲሆን የዚህም መገለጫው በክልሎች ከዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ከቀበሌ መስተዳድር ጀምሮ እስከ ክልል ምክር ቤት ያሉ የመንግሥት አካላት የሚቋቋሙት በሕዝብ ምርጫ ሲሆን በፌዴራል ደረጃ ያሉትም ሁለት ምክር ቤቶች (የሕዝብ ተወካዮችና የፌዴሬሽን) የሚመሠረቱት ሕዝቦች መርጠው በሚልኳቸው ወኪሎቻቸው አማካኝነት መሆኑ ነው፡፡

የሕዝብ ሉዓላዊነት ሁለተኛው መገለጫ ሕዝቦች በቀጥታ የሚያደርጉት ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ሲሆን በዚህም መሠረት ሕዝቦች በየአካባቢያቸው እንዲሁም በተለያዩ ደረጃዎች መንግሥት በሚያዘጋጃቸው የልማት ዕቅዶችና ፖሊሲዎች ላይ በመወያየት አፈጻጸማቸውን በመከታተልና በመገምገም በጉዳዮች ላይ በመምከር እንዲሁም ሕጎች በሚወጡበት ጊዜ የተለያዩ አስተያየቶችንና ሃሳቦችን በማቅረብ ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡

የሕዝብ ሉዓላዊነት ሌላው ዐቢይ መገለጫ አንድ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል ያለውን መብቱን ተግባራዊ የሚያደርግበት አካሔድ ነው፡፡ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 39/1-3/ በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሠረት ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ ለመወሰን በቋንቋው የመፃፍ፣ የመናገር፣ ቋንቋውን የማሳደግ፣ ባሕሉን የመግለጽ የማዳበር፣ ታሪኩን የመንከባከብ እንዲሁም በሰፈረበት መልክዓ ምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋማት

የማቋቋም በክልልና በፌዴራል ደረጃ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብቱ ተረጋግጧል፡፡ በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /4/ የተቀመጠው ደግሞ አንድ ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ የመገንጠል መብቱን ሥራ ላይ ለማዋል አስቀድሞ የወከለው የሕግ አውጪ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ከደገፈው በኋላ ብሔር፣ ብሔረሰቡና ሕዝቡ በቀጥታ በሕዝበ ውሳኔ ተሳትፎ እንዲደግፈው ይደርጋል፡፡ በተጨማሪም የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሀሳብ ለማቅረብ በየደረጃው ባሉና በምርጫ ባቋቋሚቸው ምክር ቤቶች አማካኝነት ተሳትፎ ማድረግ የሚችሉበት ሥርዓት በሕገ መንግሥቱ ተደንግጓል፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ የሕግ ማዕቀፎችና ሒደቶች የሚያሳዩት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በሀገራችን የሥልጣን ምንጭና ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤቶች መሆናቸውንና ሕገ መንግሥቱም የሉዓላዊነታቸው መገለጫ መሆኑን ነው፡፡

### 4.2.2. የሕገ መንግሥት የበላይነት

ሁለተኛው መርህ የሕገ መንግሥት የበላይነት ሲሆን በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9 በዝርዝር ተደንግጎ እናገኘዋለን፡፡ ድንጋጌው:-

1. *ሕገ መንግሥቱ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ ነው፡፡ ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሰራር እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡*
2. *ማንኛውም ዜጋ የመንግሥት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች ሌሎች ማኅበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው ሕገ መንግስቱን የማስከበርና ለሕገ መንግሥቱ ተገዢ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው፡፡*

3. *በዚህ ሕገ መንግሥት ከተደነገገው ውጪ በማናቸውም አኳኋን የመንግሥት ሥልጣን መያዝ የተከለከለ ነው፡፡*

በማለት ይገልፃል፡፡ የሕገ መንግሥት የበላይነት አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት እንደ አጠቃላይ በሚከተሉት ሁኔታዎች መገለጽ ይችላል፡፡ ሕገ መንግሥቱ የሕዝብን ፍላጎት እና ፈቃድ የያዘ የመንግሥት ሥልጣን ይዘት፣ አደረጃጀት እና ክፍፍል ምን እንደሚመስል የሚገልጽ በመንግሥትና በዜጎች መካከል የሚኖረውን የግንኙነት መልክ የሚወስን፣ መንግሥት የሚከተላቸውን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መርሆዎች፣ ፖሊሲዎችና አቅጣጫዎች የሚያመላክት በአጠቃላይ የሕዝቡን ዕድልና ሕይወት የሚነኩ ጉዳዮች ያሉበት ሰነድ ስለሆነ ነው፡፡

በኛ ተጨባጭ ሁኔታ ባለፈው ታሪካችን በነበሩ ሥርዓቶች የሕግ የበላይነት ያለመኖር ለአምባገነንነት መስፈንና ለዴሞክራሲ እጦት ምክንያት የነበረ በመሆኑ ይህንን ሁኔታ ሥር ነቀል በሆነ መንገድ መቀየር የግድ ስለሆነ እንዲሁም የፌዴራላዊ የፖለቲካ ሥርዓት የምንከተል በመሆኑ የሕገ መንግሥት የበላይነቱን ልዩ የሚያደርገው ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የስልጣን ባለቤቶች መሆናቸውን መሠረት በማድረግ የመንግሥትን ሥልጣን በፌዴራልና በክልል ያከፋፈለበት፣ የሁለቱንም ሥልጣንና ተግባር የወሰነበት የፌዴራል ሥርዓታችን የተዋቀረበትና የተደራጀበት አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሕጋዊ ስርዓታችን የተገነባበትና የተመረኮዘበት የሕግ ማዕቀፍ ስለሆነ ነው፡፡

ከላይ እንዳየነው ሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 9 ስለሕገ መንግሥት የበላይነት ሲደነግግ ሶስት መሠረታዊ ሀሳቦችን ያስቀምጣል፡፡ እነዚህንም ሀሳቦች ዘርዘር አድርገን እንደሚከተለው እንመለከታቸዋለን፡፡ በፌደራሉ መንግሥት ሥልጣን ሥር ባሉ ጉዳዮች ላይ እፀፅ በርካ□ ሕጐች ወጥተዋል ወደፊትም ይወጣሉ፡፡ በክልሎች □ረጃም በርካ□ ሕጎች ወጥተዋል ወደፊትም ይወጣሉ፡፡ □□ዴራሉም ሆነ የክልል ሕገ መንግሥት ሕፅ እንደመሆናቸው መጠን በአፈፃፀም ወቅት የሕጐች አለመጣጣም ሊከሰት ስለሚችል የትኛው የበላይነት ይኖረዋል የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡

በግልጽ እንደተቀመጠው የኢትዮጵ□ □□ራላዊ ዴሞ□ራሲ□ዊ ሪዩብሊ□ ሕ□ መንግሥት የሀ□ሪቱ □በላ□ ሕግ ነው፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ሕፅ፣ ልማ□ዊ አሠራር፣ እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ ጋር የሚቃረን ከሆነ ተ□ፃሚነት አይኖረውም፡፡ □□ዴራሉ ሕገ መንግሥት የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ በክልል ደረጃ የክልሉ ሕገ መንግሥት የክልሉ የበላይ ሕፅ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ የአትዮጵ□ □□ራላዊ ዴሞ□ራሲ□ዊ ሪዩብሊ□ ሕ□ መንግሥት በአንድ ክልል የሚኖሩ ሕዝቦች በሌሎች ክልሎች ውስጥ ከሚኖሩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጋር በመስማማት ያለውን አንድነት ለማጠናከርና ሌሎች ዓላማዎችንና □ምነቶችን ለማሳካት ለገቡት ስምምነት ማሠሪያ ሰነድ መሆኑን ከዚህ በፊት ለማየት ሞክረናል፡፡ በመሆኑም የሀ□ሪቱ ሕገ መንግሥት ከአጠቃላይ ጉዳዮች አንፃር ሲታ□ □ሀ□ሪቱ □በላ□ ሕግ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይህ የበላይነት እንዳለ ሆኖ በዚያው ሕገ መንግስት ድንጋጌ መሠረት የክልል መንግሥታት የየራሳቸውን ሕገ መንግሥት ማውጣት □ንደሚችሉና የሚወጣውም ሕገ መንግሥት የጋራ ይሁንታ ካ□ኘውና የስምምነታቸው ማረጋገጫ ከሆነው የፌዴራሉ ሕ□ መንግሥት ጋር መቃረን የሌለበት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

ሕገ መንግሥት የበላይ ሕግ ከመሆኑ የተነሣ ማናቸውም ሕግም ሆነ ልማዳዊ አሠራር ከሕገ መንግሥቱ ጋር የሚቃረን ሆኖ ሲገኝ ተፈፃሚነትን ያጣል:: በ□ዴራልም ሆነ በክልል ሕግ የማወጣትም ሆነ የማስፈፀም የመንግሥት ሥልጣን በሀገሪቱና በክልሎች የሚኖሩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በጋራ ስምምነትና ይሁንታ የሰጡትና የፈቃዳቸው መገለጫ መሆኑን አይተናል:: በመሆኑም በውክልና ሕግ የማውጣት ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት አካል የሚያወጣው ሕፅ ውክልናውን ከሰጠው ወካይ መልካም ፈቃድ ጋር የሚቃረን ሕፅ ቢ□□□ □□□□ ሕፅ ተ□ፃሚነት እንዳይኖረው ማድረግ አግባብነት ያለው መሆኑን ማየት ይቻላል:: ስለ□ህ ማንኛ□ም ሕግ፣ ልማዳዊ አሠራር፣ □ንዲሁም የመንግሥታዊ አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ ጋር የሚቃረን ሆኖ ሲገኝ ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑ በሕ□ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) በግልጽ ተደንግጓል:: በሕገ መንግሥቱ የተካተቱ የጋራ ጥቅሞችን የሚቃረን ሁሉ በሕገ መንግሥቱ ላይ የበላይነት ሊኖረው አይገባም:: ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ዋነኛ ነጥብ የሕገ መንግሥቱ የበላይነት የሚመነጨው ከሕዝቦች ሉዓላዊነትና ቀዓ ተኛ ዓ ቅም ነው::

በሁለተኛ ደረጃ ማንኛውም ሰው፣ የመንግሥት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሌሎች ማኅበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው ሕገ መንግሥቱን የማክበርና ለሕ□ መንግሥቱ ተገዥ የመሆን ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑ ከላይ በተ□ለ□□ □ሕ□ መንግሥቱ አንቀጽ ተደንግጓል:: ከዚህ ድንጋጌ በዋናነት የምንገነዘበው ነገር ቢኖር ማናቸውም በፌዴራልም ሆነ በክልል የሚገኝ ግለሰብም ሆነ የመንግሥት አካል ሕ□ መንግሥቱን የማክበርና የማስከበር ፅ□ታ ያለበት መሆኑን ነው:: በሕገ መንግሥቱ የተካተቱ ድንጋጌዎችን የማይቀበል ቢሆንም እንኳን ለሕገ መንግሥቱ የመገዛት ፅ□ታ አለበት:: ይህ ድንጋጌ በግልጽ የሚያሳየን ማንም ባለሥልጣንም ሆነ ዜጋ

ባለፉት ሥርዓቶች እንደነበሩት ገዢዎች ከሕግ በላይ መሆን የሚችልበት ዕድል እንደሌለና ልዩነት ሳይኖር ሁሉም ከሕገ መንግሥቱ በታች መሆናቸውን ነው። □ህ □ፅሞ በሀ□ሪቱ የሁሉም ሥልጣን ባለቤት የሆኑት የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ውሳኔ እንደመሆኑ መጠን ገዥ የሆነ ግዴታ መሆኑን እንገነዘባለን። የተለያየ □ፖለቲካ አቋምና መርህ ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲሁም የተለያዩ ተግባራትን የሚ□ጽሙ ማኅበራትና ባለስልጣኖቻቸው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ፍላጎትና ጥቅም ቅድሚያ የመስጠትና የማክበር ግዴታ የተጣለባቸው መሆኑን ጭምር እንገነዘባለን።

□ሕገ መንግሥቱ የበላይነት ጽንሰ ሀሳብ ሌላ□ው መ□ለ□ በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉ የመንግሥት ሥልጣን የሚያዝባቸው ሥርዓቶችን ማክበር ነው። በሀገራችን የመንግሥት ስልጣን የሚያዘው ዴሞክራሲያዊ፣ ሁሉ አቀፍ፣ ነፃና ፍትሐዊ በሆነ የምርጫ ሥርዓትና ውድድር ሲሆን የመንግሥት ሥልጣን የሚረከበውም አካል በዴሞክራሲያዊ አግባብ የመራጩን ይሁንታ እና ፈቃድ ያገኘ የፖለቲካ ፓርቲ ነው። ከዚህ ውጪ የመንግሥት ሥልጣን ለመያዝ የሚደረግ ሙከራና እንቅስቃሴ ሁሉ የሕዝቦች የሉዓላዊነት መገለጫ የሆነውን ሕገ መነግሥት መፃረር በመሆኑ ተቀባይነት የለውም።

በአጠቃላይ ሕገ መንግሥቱን ማክበር፣ በሕገ መንግሥቱ የመመራትና ለሕገ መንግሥቱ መገዛት አንዱ ሕገ መንግሥታዊ መርህ መሆኑ ግልጽ ከሆነ ይህ መርህ በተሟላ ሁኔታ እንዲተገበር በድንጋጌዎቹ ላይ በቂ ግንዛቤ መያዝ ያስፈልጋል። በቂ ግንዛቤ እንዲኖር ደግሞ የተጠናከረ ግንዛቤ መፍጠር፣ የመማርና የማስተማር ስራዎች በስፋትና በጥልቀት መስራት ያስፈልጋል።

### 4.2.3. ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች

የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር መሠረቱ ተደንግጎ የምናገኘው በአንቀጽ 10 ሲሆን ድንጋጌዎቹ እንደሚከተለው ይነበባሉ፡-

1. *ሰብዐዊ መብቶችና ነጻነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ፣የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው፣*
2. *የዜጎች እና የሕዝቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ይከበራሉ*

የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበርና ሕገ መንግሥታዊ ዋስትና ማግኘታቸው ሶስተኛው የሕገ መንግሥቱ መሠረታዊ መርህ ነው፡፡ ሕገ መንግሥታችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ ያደረገበት ዋናው ምክንያት እነዚህን መብቶች ለማስከበር የተከፈለው መስዋዕትነት፡ የተካሔደው ትግልና የትግሉ ውጤት እንዲሁም የተገኘው ሰላም በዘላቂነት እንዲቀጥል፣ ሁሉም ዜጐችና በተለይም ተረስተው የነበሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በሁለንተናዊ መልኩ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው፡፡

በሕገ መንግሥቱ መግቢያ ላይ እንደተመለከተው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በነፃ ፈቃዳቸው እና በሕግ የበላይነት ላይ በመመስረት አንድ የፖለቲካ እና የፖለቲካ ማኅበረሰብ ለመገንባት ለያዙት ዓላማ መሳካት የግለሰብና የብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ መሠረታዊ መብቶች መከበራቸው አስፈላጊ መሆኑን አጽንዖት ሰጥተውበታል፡፡

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥትም የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሕገ መንግሥት ሆኖ የቅርብ ጊዜ የሰዎችና የኅብረተሰብ ዕድገት በተሻሻለበት ወቅት □□□ እንደመሆኑ መጠን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኙትን የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በመቀበል አንዱ መሠረታዊ መርሆ ያደረገበትን ሁኔታ

እናገኛለን፡፡ በዚህም መሠረት ሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች የመንግሥት ወይም የባለስልጣናት ችሮታ ሳይሆኑ ከተፈጥሮ የሚመነጩ እንደመሆናቸው የማይጣሱና የማይገፈፉ መሆናቸውን በመገንዘብ ሕገ መንግሥቱ ለመሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች የተለየ ሥፍራ የሚሰጥ መሆኑን እንረዳለን፡፡

ለዚህም ዋነኛ ማሳያዎች:-

- በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌና ስምምነቶች ውስጥ ከተካተቱ መብቶችና ነፃነቶች ዋና ዋናዎቹ በሕገ መንግሥቱ የተካተቱ መሆናቸው፣
- □ሕገ መንግሥቱ ምዕራፍ ሶስት መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በሚተረጐሙበት ጊዜ ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት፣ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና ሠነዶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ እንዲሆን መደንገጉ፣ እና
- በሕገ መንግሥቱ ምዕራፍ ሦስት ውስጥ የተካተቱ መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ሊሻሻሉ የሚችሉት እንደ ተራ ሕግ በቀላሉ ሳይሆን ወይም እንደ ሌሎች የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ቀለል ባለ ሥርዓት ሳይሆን ጠንከርና ወሰብሰብ ባለ ሥርዓት መሆኑን የ□□ራሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 105 (1) ድንጋጌዎች ስለሚያሳይ ነው::

ከዚሁ ጋር መነሳት ያለበት አንዱ ነጥብ ሕገ መንግሥታችን በተለየ ሁኔታ ሌሎች ህግጋተ መንግሥት ደፍረው ያልደነገጉትን ሀሳቦች በመደንገግ ዜጐች በሃይማኖታቸው ወይም በባሕላቸው የመዳኘት፣ የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን እስከ መገንጠል ያሉ መብቶችን እንዲከበሩ ዋስትና ሰጥቷል፡፡ በሌላም በኩል ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበራቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል ሕገ መንግሥቱ በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራልና የክልል የመንግሥት አካላት እነዚህን ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ እንዳለባቸው መደንገጉ ግንዛቤ ሊያዝበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

### 4.2.4. የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት

ሕገ መንግሥታችን በአንቀጽ 11 ስለመንግሥትና ሃይማኖት መለያየት የደነገገው አንዱ መርህ ሲሆን ድንጋጌው፡-

1. መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው፡፡
2. መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም፡፡
3. መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡ ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም ይላል፡፡

በሕገ መንግሥቱ በግልጽ እንደተቀመጠው □□ዴራልም ሆነ የክልል መንግሥት በሀገርና በክልል ደረጃ የሕዝቦች ተወካይ ሆነው የሕዝቦቻቸውን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ጥቅሞችና ፍላጎቶች የሚያስከብሩ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል በሀ□ራችን □ስዓ □ተለ□□ እምነቶች የሚገኙ ቢሆንም የእምነትና ሃይማኖት ጉዳይ □ግለሰቦች ምርጫ መሆኑ ለሁሉም ግልጽ ነው፡፡ ሃይማኖት የግለሰቦች የግል ምርጫ እንደመሆኑ መጠን መንግሥት በግለሰቦች የሐይማኖት ጉዳይ ላይ ጣልቃ እንዲገባ የሕገ መንግሥቱ ባለቤቶች የሆኑት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፍላጎት አይደለም፡፡ በመሆኑም መንግሥት በተወካይነቱ በሃይማኖት ጉዳይ ላይ በተመሳሳይም ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ እንዳይገቡ የተደረገበት መነሻ ሀሳብና ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 11 ድንጋጌዎች የምንረዳው ይህንኑ ነው፡፡

በየትኛውም የዓለም ክፍል የመንግሥት የተለመዱ ተግባራት አሉ፡፡ ዋነኛዎቹ የመንግሥት ተግባራት የሕዝቡን ሠላምና ደኅንነት ማስከበር፣ ግብር መጣልና መሰብሰብ፣ ለሕዝቡ አስፈላጊ የሆኑ ዋና ዋና አገልግሎቶችን ማቅረብና ሕዝቡን ከውጪ ወራሪ መከላከል ናቸው፡፡ እነዚህንና ሌሎችን የመንግሥት ተግባራት ለመ□□ም □ሃይማኖትና የመንግሥት ግንኙነት ፋይዳ ላይኖረው ይችላል፡፡ አንዳንድ

□□ □እንዲያውም የሁለቱ ግንኙነት የሕዝቡን ሠላምና ደኅንነት የሚያውክ ስለሚሆን በሁለቱ መካከል ልዩነት መኖሩ □ቃሚ ይሆናል፡፡ በተለይ በእኛ ሁኔታ የሃይማኖት ብዝሀነት ቢኖርም ባለፉት መንግሥታት በተለይም በአፄው ዘመን መንግሥትና ሃይማኖት ሳይነጣጠሉ አንድ በነበሩበትና እስከ አሁንም በሃይማኖቶች መካከል ያለው ቁርሾ አልፎ አልፎ በሚታይበት ሁኔታ መንግሥት ለሁሉም ሃይማኖቶች እኩል ክብር ሰጥቶና በሃይማኖት ጉዳይ ሳይገባ ተግባራቱን በነፃነት ማከናወኑ እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡

በይበልጥም በሕገ መንግሥታችን የእምነት ነፃነትና የሃይማኖቶች እኩልነት ካለ አንዳች ልዩነት መከበራቸው ዋስትና በተሰጠበት ሁኔታ መንግሥታችን እንደ መንግሥት ፖለቲካና ሃይማኖትን ሳያደበላልቅ ለመብቶቹ መከበር ይሰራል፡፡ ሌሎችም የፖለቲካ ኃይሎች ይህንኑ እንዲከተሉ ያደርጋል፡፡ በሌላ በኩል በሀገራችን ያሉ የሃይማኖትና የእምነት ተቋማትም በዚሁ መርህ መገዛት ስላለባቸው በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ ሳይገቡ ሃይማኖታው ተግባራቸውን ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ስለሆነም በሀገራችን ሁኔታ ፖለቲካ የሃይማኖት ሃይማኖትም የፖለቲካ መድረክ ሊሆኑ የሚችሉበት ሁኔታ የለም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ መንግሥት የሕዝብን ሰላም፣ ደኅንነት፣ ሞራል እና የሌሎች ዜጎች መብቶችን ለመጠበቅ ሲል አግባብ ባላቸው ሕጎች በመመራት የሃይማኖትና እምነትን የመግለጽ መብት እንዲገደብ ሊያደርግ የሚችልበት አግባብም እንዳለ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በአጠቃላይ ሕገ መንግሥታችን የተለያዩ ሃይማኖቶችና እምነቶች ባሉበት ሀገርና ሁኔታ ሁሉም ሃይማኖቶች ከመንግሥት ነፃ ሆነው በእኩልነትና በመቻቻል እንዲኖሩ የመንግሥትና የሃይማኖቶች ልየነት እንዲጠበቅ ማድረጉ በሳልና ዘመናዊ ሕገ መንግሥት ያለን ለመሆኑ ጉልህ ማሳያ፡፡

## 4.2.5. የመንግሥት አሠራርና ተጠያቂነት

አምስተኛው መርህ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 12 የተደነገገውና የመንግሥትን አሠራርና ተጠያቂነት የሚመለከተው ሲሆን ድንጋጌው፡-

1. *የመንግሥት አሠራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት፡፡*
2. *ማንኛውም ኃላፊና የሕዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል፡፡*
3. *ሕዝብ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ለማንሳት ይችላል፡፡ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል ይላል፡፡*

በ□ዴራልም ሆነ በክልሉ መንግሥት እና በሕዝቡ መካከል ያለው ግንኙነት የወካይና የተወካይ /እንደራሴ/ ግንኙነት መሆኑን ሕገ መንግሥቱ ካስቀመጣቸው ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡፡ በ□ዴራል □ረጃ □ሀገሪቱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ወካይ ሲሆኑ የፌዴራሉ መንግሥት ተወከይ ይሆናል፡፡ በክልል ደረጃም በክልሉ የሚኖሩ ሕዝቦች ወካይ ሲሆኑ የክልሉ መንግሥት ደግሞ እንደራሴ ነው፡፡ በማንኛውም የተወካይነት (እንደራሴነት) ግንኙነት ተወካዩ (እንደራሴው) ለሚፈጽመው ተግባር ሥልጣን የሚያገኘው ከወካዩ ነው፡፡ ሥልጣንን ብቻ ሳይሆን አስፈላጊውን ሀብትም የሚያገኘው ከወካዩ ነው፡፡ ለዚህ ዋነኛ□ ምክንያት ተወካዩ የሚፈጽመው ድርጊት በራሱ ስም ለራሱ ጥቅም ሳይሆን ለወከለው ግለሰብ ወይም ሌላ አካል ጥቅም ስለሆነ ነው፡፡

□□ዴራሉንም ሆነ የክልሉን መንግሥት የወከለው ሕዝብ ተወካዩ የተሰጠውን ሀብትና ሥልጣን በአግባቡ ለተባለለት ሥራና አገልግሎት ማዋሉን ለማየትና ለማወቅ ፍላጐት ይኖረዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተወካዩ ድርጊቶችና እንቅስቃሴዎች ወካዩ ባዘዘውና በሚፈልገው መንገድ መሆን አለበት፡፡ ይህንን ለማረ□□ፃ □ተ□ካ□

ሥራዎችና እንቅስቃሴዎች ለወከለው አካል ግልጽ መሆን ይኖርባቸዋል:: ከዚህ መርህ በመነሳት የፌዴራሉም ሆነ የክልል ሕገ መንግሥታት የመንግሥት አሠራርና ተጠያቂነትን እንደ አንድ ዋነኛ መሠረታዊ □ሕገ መንግሥቱ መርሆዎ አድርጎ ደንግጓል::

የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 12 ድንጋጌ መሠረት የፌዴራሉ መንግሥት አሠራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት:: በሌላ አነጋገር የተወካዩ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ከወካዩ የተሠወረ መሆን የለበትም:: የሀ□ሪቱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የፌዴራሉን መንግሥት የወከሉና በሀ□ሪቱ □ስዓ □ሁሉም ሥልጣንና ሀብት ባለቤት እንደ መሆናቸው መጠን በእነርሱ ስምና ለራሳቸው ዓቅም የሚከናወኑ የመንግሥት ተግባራት ግልጽ ሊሆኑላቸው □□ባል:: የሉዓላዊ የሥልጣን ባለቤቶች በመሆናቸውም በውክልና ተግባራትን የሚያከናውነው መንግሥት አካላትና በመንግሥት ስራ ላይ የተሰማሩ ዜጎች ተገቢውን አክብሮት ሊሰጧቸው ስለሚገባ ተግባሮቻቸውን ለወከላቸው ሕዝብ ግልጽ የማድረግ ግዴታ አለባቸው::

ከላይ የተገለፀው አንቀጽ ሌላው ድንጋጌ ሕዝቡ ተወካዩን ከቦታ□ □ሚ□ነሣበት ሁኔታ ነው:: የፌዴራሉ መንግሥትና ሌሎች አካላት የሕዝቡ ተወካይነት ሊቆይ የሚችለው ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በወከሉት ተ□ካ□ ላ□ እምነት ሲኖራቸው ብቻ ነው:: የውክልና ግንኙነት ፀንቶ መቆየት የሚችለው የተወከለው የወከለውን አካል ፍላጐትና ጥቅም በአግባቡ ሲያሟላና ሲጠብቅ እንደመሆኑ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕ□ቦች ተወካዮቹ ፍላጐታቸውንና ጥቅማቸውን የማይጠብቁና የማያስከብሩ ሆነው ሲያገኙዋቸው በማንኛውም ጊዜ ውክልናውን በማንሳት ግንኙነቱን ሊያቋርጡ ይችላሉ:: የተወካዩ ተግባርና እንቅስቃሴ ወካዩ

ዝርዝሮ በሰጣቸው ሥልጣናትና ተግባራት ክልል ብቻ መሆን አለበት፡፡ የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት የፌዴራሉ መንግሥትና የተለያዩ አካላት ሥልጣንና ተግባራት ምን እንደሆነ በዝርዝር ያስቀምጣል፡፡ ከዚህ ተዘርዝሮ ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር □·□ የሚንቀሳቀስ ከሆነ የፌዴራሉ መንግሥትም ሆነ ሌላ አካል የሀገሪቱን ሕ□ብ ጥቅምና ፍላጐት ሊያሟላ አይችልም፡፡ በዚህ ጊዜ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በወከሉት አካል ላይ እምነት በማጣት ውክልናውን ለማንሳት ይችላሉ ምክንያቱም በሀ□ሪቱ □ላ□ የሥልጣን ባለቤቶች በመሆናቸው ነው፡፡

በሌላ በኩል ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በወከሉት አካል ላይ እምነት ባጡ ጊዜ ውክልናውን ከማንሳት ሌላ ተወካዩ ኃላፊነቱን በተገቢው ሁኔታ ካልተወጣ ውክናውን በማንሳት ተጠያቂ የማድረግ መብት ያላቸው መሆኑን የዚሁ ድንጋጌ ሃሳብ ያስረዳል፡፡

## 4.3. የብሔራዊ ፖሊሲ መርሆዎችና ዓላማዎች

ሕገ መንግሥቱ በምዕራፍ አስር ከአንቀጽ 85 - 92 ባሉት ድንጋጌዎች ቀደም ሲል ካየናቸው መሠረታዊ መርሆዎች ሌላ የመንግሥትና የኅብረተሰቡን ኃላፊነትና ጥቅም በወሳኝነት የሚነኩ ሰባት ዐበይት የተኩረት መስኮችን የብሔራዊ ፖሊሲ መርሆዎችና ዓላማዎች አድርጎ አስቀምጧቸል፡፡ እነደመነሻም ማናቸውም የፌዴራልም ሆነ የክልል መስተዳድር አካላት እና ባለሥልጣኖች ሕገ መንግሥቱንና ሌሎች ሕጎችን ስራ ላይ ሲያውሉ በእነዚህ መርሆዎችና ዓላማዎች መመራት እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡ እነዚህንም እንደሚከተለው በአጭሩ እንመለከታቸዋልን:-

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት
The House of Federation of the Federal Democratic Republic of Ethiopia
1995

### 4.3.1. የውጭ ግንኙነት መርሆዎች

ከመርሆዎቹ የመጀመሪያው የውጭ ግንኙነትን የሚመለከት ሲሆን መርሁ የተመሠረተው የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት፣ የሕዝቡን ጥቅም በመጠበቅ እና የውጭ ግንኙነቶችን በማራመድ ላይ ሲሆን አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ከጎረቤት ሀገራት ጋር ጥብቅ ኢኮኖሚያዊ ትስስር በመፍጠር ላይ ያተኮረ ነው፡፡

### 4.3.2. የመከላከያ መርሆዎች

በሁለተኛ ደረጃ የተቀመጡት ብሔራዊ የመከላከያ መርሆዎች ናቸው፡፡ በመርሆዎቹ ውስጥ የተካተቱት ሀሳቦች የመከላከያ ኃይሉ ለሕገ መንግሥቱ ተገዢ መሆን እንዳለበት፣ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጠን መንግሥት ማገልገል እንዳለበት እና ታማኝነቱም ለሕገ መንግሥቱ እንጂ ለፖለቲካ ፓርቲ ወይም ፓርቲዎች መሆን እንደሌለበት የሚገልጹ ናቸው፡፡

ከብሔራዊ ፖሊሲ መርሆዎች በመቀጠል ሕገ መንግሥቱ ያስቀመጣቸው የመንግ ሥትን ኃላፊነት የሚመለከቱና መንግሥት ሊተገብራቸው የሚገቡ ዓላማዎችን ነው፡፡ እነዚህም በአጭሩ ፖለቲካ ነክ፣ ኢኮኖሚ ነክ፣ ማኅበራዊ ነክ፣ ባሕል ነክ እና የአካባቢ ደኅንነትና ጥበቃ ዓላማዎች ሲሆኑ ዘርዘር አድርገን እንደሚከተለው እንመለከታቸዋለን፡፡

### 4.3.3. ፖለቲካ ነክ ዓላማዎች

እነዚህ ዓላማዎች በጥቅሉ የያዟው ሀሳቦች በሕገ መንግሥቱ ከመግቢያው ጀምሮ መሠረታዊ መብቶችን የመንግሥት አካላት ሥልጣንና ተግባራትን በሚመለከቱ ድንጋጌዎች ውስጥ ተሰራጭተው የሚገኙ ናቸው፡፡ እነዚህ ዓላማዎች መንግሥት

መሠረታዊ የፖለቲካ እሴቶችን ለማዳበር ግዴታውን እንዲወጣ አቅጣጫ የሚሰጡት ናቸው፡፡ በእነዚህ ዓላማዎች መሠረት አንደኛ መንግሥት በዴሞክራሲያዊ መርሆዎች በመመራት ሕዝቡ በየደረጃው ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት ያለበት ሲሆን ይህም የሀገሪቱን ፖለቲካዊ ሒደት ለመቀየርና የፌዴራል ሥርዓቱን ለማጠናከር ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ መንግሥት የብሔሮችን፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን የማክበርና በመካከላቸው እኩልነት፡ አንድነትና ወንድማማችነት እንዲጠናከር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

### 4.3.4. ኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች

በኢኮኖሚ አቅጣጫ የተቀመጡት ዓላማዎች ትኩረታቸው በፍትሐዊ የብሔራዊ የሀብት ክፍፍል ላይ ሲሆን በዚሁ መሠረት መንግሥት ትክክለኛ ፖሊሲዎችን በመቅረጽ ያለ አንዳች ልዩነት ሁሉም ኢትዮጵያውያን የሀገሪቱ የተጠራቀመ እውቀትና ሀብት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን እንዲያመቻች ግዴታ ያስቀመጡበት መሆኑን እንረዳለን፡፡ ማንም ሰው የዚህን መሠረታዊ ዓላማ አስፈላጊነት የሚረዳው የሀገሪቱን ያልተነካና እምቅ ሀብት እንዲሁም ሕዝቡ የሚገኝበትን ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ በአንድ ላይ በማነፃፀር ሲመለከተው ነው፡፡ በእነዚህ ዓላማዎች ላይ በመመስረት መንግሥት የሀገር ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ እንዲከፋፈል የማድረግ፣ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች እንዳይደርሱ የመከላከልና ሲደርሱም ተገቢውን እርዳታ የማድረግ፣ በእድገት ወደኋላ ለቀሩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ልዩ ድጋፍ የማድረግ፣ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን በሕዝብ ስም በማስተዳደር ለሕዝቡ የጋራ ጥቅምና እድገት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ሀገራዊ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በሚዘጋጁበት

ወቅትም ሕዝቡ እንዲሳተፍ ማድረግና በሕዝቡ አቅም የሚደረጉ የልማት እንቅስቃሴዎችንም መደገፍ እነዚህ ኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች ለመንግሥት ያስቀመጡት አቅጣጫ ነው። የእነዚህ ዓላማዎች አተገባበር ውጤት ነው ዛሬ ሀገራችን በሁሉም ዘርፎች ፈጣን እና ሁሉም ዜጎች ተጠቃሚ እየሆኑ ያሉበትን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገት ለማስመዝገብ ያስቻላት።

### 4.3.5. ማኅበራዊ ነክ ዓላማዎች

በማኅበራዊ ነክ ዓላማዎች በመመራት መንግሥት አቅሙ በፈቀደ መጠን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ የንጹህ ውኃ፣ የምግብ፣ የመኖሪያና የማኅበራዊ ዋስትና እንዲኖረው እንደሚያደርግ አቅጣጫ ተቀምጧል። የእነዚህ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎች ውጤት ነው ዛሬ ትምህርት እንደ ልዩ መብትና እድል ይቆጠርባት በነበረ ሀገር ሁሉም ሕፃናት ትምህርት ቤት እንዲገቡ የመጀመሪያ ደረጃ፣ የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ እንዲስፋፋ እየተደረገ ያለው። እነዚህ ዓላማዎች በተለይ ትምህርት ትውልድንና ኅብረተሰብን ለመቅረጽ ከፍተኛ ሚና ያለው መሆኑን ከግምት በማስገባት ትምህርት በማናቸውም ረገድ ከሃይማኖት፣ ከፖለቲካ አመለካከቶችና ባሕላዊ ተጽዕኖዎች ነፃ በሆነ መንገድ መካሔድ እንዳለበት ያስቀምጣሉ። በዚህ ላይ የሕገ መንግሥቱ ዓላማ ተማሪው ትምህርትን በነፃ የማሰቢያና መረጃ የማግኛ መሳሪያ በማድረግ በራሱ የሚወስን ዜጋ ለማድረግ እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

### 4.3.6. ባሕል ነክ ዓላማዎች

በእነዚህ ዓላማዎች መሠረት መንግሥት መሠረታዊ መብቶችን፣ ሰብዓዊ ክብርን፣ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብንና ሕገ መንግሥቱን የማይቃረኑ ባሕሎችና ልማዶች

በእኩልነት እንዲያድጉና እንዲስፋፉ የመርዳት ኃላፊነት አለበት፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ሕገ መንግሥቱ ስለማኅበራዊ ነክ ዓላማዎች አስፈላጊነት ለማሳየት የሚነሳው መንግሥት መሠረታዊ መብቶችንና ሰብዓዊ ክብርን የመጠበቅና የማክበር ኃላፊነት እንዳለበት በማስታወስ ነው፡፡ ሕገ መንግሥቱ በብዙ ቦታዎች ለመሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች የሚሰጠው ትኩረት በስፋት የተገለፀ ሲሆን የዚህ ክፍል ዋናው ትኩረቱ ሰብዓዊ መብቶችን የማክበርን ባሕል መሠረት መጣል ላይ ነው፡፡

በእነዚሁ ዓላማዎች ስር ትኩረት የተሰጠባቸው ሌሎች ጉዳዮች መንግሥት አቅሙ በፈቀደ መጠን ኪነጥበብን፣ ሳይንስንና ቴክኖሎጂን እንዲያስፋፋ ግዴታ ያለበት መሆኑን የተመለከቱና ዜጎችም የተፈጥሮ ሀብትንና የታሪክ ቅርሶችን የመጠበቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው የሚያስገነዝቡ ናቸው፡፡

## 4.3.7. የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ ዓላማዎች

በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ሀገራትና መንግሥታት አስፈላጊነቱ እየታመነበትና ትኩረት እየሳበ ያለ ጉዳይ የአረንጓዴ ልማት የእድገት አቅጣጫ ነው። ይህ አስተሳሰብ በሕገ መንግሥታችን ከ17 ዓመታት በፊት ቀድሞ የታየ ሲሆን ሕገ መንግሥቱ ባስቀመጣቸው የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ ዓላማዎች የተንፀባረቀ ጉዳይ ነው። በእነዚህ ዓላማዎች መነሻነት መንግሥት ሁሉም ዜጎች በንጹህና ጤናማ አካባቢ እንዲኖሩ የመጣር ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ማናቸውም የኢኮኖሚ ልማት እርምጃ ከአካባቢ ደህንነት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ያስፈልጋል። እዚህ ላይ ማናቸውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በሚደረጉበት ጊዜ የአካባቢ ደህንነትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ትክክለኛ ደንቦችና መመሪያዎች መኖራቸውንና ስራ ላይ መዋላቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት የመንግሥት መሆኑን መረዳት ይቻላል። ይህ ሕገ መንግሥታዊ አቅጣጫ መተግበር

በእድገት ጅማሮ ላይ ላለች ሀገራችን መልካም እድልና አጋጣሚ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ከዚሁ ጋር በእነዚህ ዓላማዎች ስር ሕገ መንግሥቱ ትኩረት የሰጣቸው ጉዳዮች የአካባቢ ደህንነት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በሚነደፉበትና ስራ ላይ በሚውሉበት ጊዜ ሕዝቡ ሀሳቡን እንዲገልጽ መደረግ ያለበት መሆኑንና ዜጎችም በበኩላቸው ከመንግሥት ጋር ሆነው አካባቢያቸውን እንዲንከባከቡ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ነው።

## 4.4. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሕገ መንግሥት ልዩ ገጽታዎች

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሕገ መንግሥት ከሌሎች ተመሳሳይ ሕግጋተ መንግሥት ጋር የሚጋራቸው የጋራ ባህርያት ቢኖሩም ከሀገራችን የተለየ ታሪካዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች በመነጨ ሁኔታ የራሱ መለያ ገጽታዎች አሉት፡፡ በተጨማሪም ሕገ መንግስቱ ቀድሞ ከነበሩት የኢትዮጲያ ሕግጋተ መንግሥት በይዘቱም ሆነ በቅርፀ ፍፁም የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ሕገመንግስቱ በመሰረታዊነት የያዛቸውን ልዩ ገጽታዎች በሶስት መልኩ እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

### 4.4.1. የብሔሮች፡ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብት

የዚህ መብት ሕገ መንግሥታዊ መሠረትና መነሻ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 39 የተደነገገው ሲሆን በዚህ ድንጋጌ እንደሰፈረው ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፡ ብሔረሰብና ሕዝብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል ያለው መብቱ በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነው፡፡ ይህንን መሠረታዊ መብት መነሻ በማድረግ ነው ሕገ መንግሥቱ ፌዴራላዊ ሥርዓቱን በአጠቃላይና የክልል

አስተዳደሮችን የመሰረተው፡፡ ይህም ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 46 እንደተደነገገው ክልሎች የተዋቀሩት በሕዝብ አሰፋፈር፣ ቋንቋ፣ ማንነትና ፈቃድ ላይ ሲሆን በክልሎች የሚገኙ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በቋንቋቸው የመናገር፣ የመጻፍ፣ ቋንቋቸውን የማሳደግ፣ ባሕላቸውን የመግለጽ፣ የማዳበርና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪካቸውን የመንከባከብ መብት አላቸው፡፡ የራሳቸውን ጉዳይ በሚመለከት እራሳቸውን የማስተዳደር በሰፈሩበት አካባቢ መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋም ሙሉ መብታቸው የተረጋገጠበትና ዋስትና ያገኘበት ሁኔታም እንዳለ መረዳት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በጋራ ጉዳዮች ላይ የጋራ የአስተዳደር ሥልጣንና ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብት ሕገ መንግሥቱ ያጎናፀፋቸው ሲሆን ይህም ሕገ መንግሥታዊ መብት ተግባራዊ መደረጉን ማሳያው በየራሳቸው የክልልና በፌዴራል ምክር ቤቶች ሚዛናዊ ውክልና እንዲኖራቸው መደረጉ እና በጋራ ጉዳዮች ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱበት ምቹ ሁኔታ መፈጠሩ ነው፡፡ ከዚሁ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብት ጋር ተያይዞ ሕገ መንግሥቱ የያዘው ልዩ ገጽታ በክልሎች ውስጥ የተካተቱት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 47/2/ እና /3/ መሠረት በማናቸውም ጊዜ የራሳቸውን ክልል የማቋቋም መብት እና ሥራ ላይ የሚውልበት አካሄድ መደንገጉ ነው፡፡

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 39 የተደነገገው ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰብና ሕዝብ እስከመገንጠል ድረስ ያለው መብቱ በማያሻማ ሁኔታ መደንገጉ ይህም አይነት ጥያቄ ቢነሳ ስራ ላይ የሚውልበትን ሂደትና ሕጋዊ ሥርዓት የደነገገ ሕገ መንግሥት መሆኑ ከላይ ከተጠቀሰው ለብሔሮች፣

ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብት ልዩ እውቅና ከመስጠት መለያ ባሕሪዩ ጋር ተያይዞ የሚታይ ነው፡፡

### 4.4.2. ሕገ መንግሥቱን የመተርጎም ሥልጣንና ተግባር

የፌዴራላዊ ሕገ መንግሥቱ ሌላው መለያ ገጽታ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 62 በመጀመሪያው ድንጋጌ እንደተመለከተው ሕገ መንግሥቱን የመተርጎም ሥልጣን ለፌዴሬሽኑ ምክር ቤት መስጠቱ ነው፡፡ በተለያዩ የፌዴራል ሥርዓቶች ለምሳሌ እንደ አሜሪካ በመሳሰሉ ሀገራት ሕገ መንግሥትን የመተርጎም ሥልጣን ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ሲሰጥ እንደ ጀርመን በመሳሰሉ ሀገራት ደግሞ ራሱን ለቻለ የሕገ መንግሥት ፍርድ ቤት ይሰጣል፡፡ የኛ ሕገ መንግሥት ግን ገና ከጅምሩ የሕገ መንግሥቱ ባለቤቶች ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መሆናቸውን ስላስቀመጠ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጉዳይ ላይ ከእነርሱ የተሻለ ተርጓሚ አይኖርም በማለት ሕገ መንግሥቱን የመተርጎም ሥልጣን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ለተወከሉበት የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሰጥቷል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ሌሎች ስድስት የሕግ ባለሙያዎችና ሶስት የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት ያሉበት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ እንደተቋም ተለይቶ በመቋቋም በትርጉሙ ስራ ምክር ቤቱን እንዲያማክርና የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ተደርጓል፡፡ ይህ ዓይነቱ በሕገ መንግሥቱ የተቀመጠው የፈጠራ ችሎታን ያገናዘበ የሕገ መንግሥት ትርጉም ሂደት የሕግና የፖሊሲ በሳል አስተሳሰቦች እንዲንሸራሸሩ እድል የሰጥ መሆኑ የሕገ መንግሥቱ ሌላው መለያ ገጽታ ነው፡፡

### 4.4.3. የመሬት ሕገ መንግሥታዊ ዋስትና ማግኘት

ሕገ መንግሥታችን ከሌሎች ሕግጋተ መንግሥት በተለይ የሊበራል ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ከሚገለጥባቸው ሥርዓቶች የሚለይበት ገጽታ መሬትን የመንግሥትና የሕዝብ ሀብት እንዲሆን ማድረጉና ለዚሁም ሕገ መንግሥታዊ ዋስትና እንዲኖር ማድረጉ ነው፡፡ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 /3/ የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ እንደሆነና መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት እንደሆነ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የመሬት ባለቤትነት መብትን በተመለከተ ሕገ መንግሥቱ በሚፀድቅበት ወቅት የተለያዩ ተቃራኒ ሀሳቦች ተንሸራሽረው የነበረ ሲሆን መሬት መሸጥ መለወጥ የለበትም የሚለው ሀሳብ አሸንፎና ገዥ ሆኖ ሊወጣ ችሏል፡፡ ይህ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ሲፀድቅ ከጀርባው የነበረው አሳማኝ ሀሳብ የመሬት ላራሹ መፈክር መሠረቱ የነበረው መሬት ገበሬው በትክክል የመጠቀምና ከመሬቱ ያለመፈናቀል መብቱ ይረጋገጥ የሚል እንጂ ገበሬው ሸጦ ለውጦ ከይዞታውና ከቀዬው ይፈናቀል የሚል አልነበረም፡፡ ከዚህ ሌላ መሬት እንዲሸጥ እንዲለወጥ ቢፈቀድና አርሶ አደሩ መሬቱን በመሸጥና በመለወጥ ኑሮው ቢናጋ እና ቢፈናቀል ሰማንያ አምስት በመቶ (85%) የሆነውን የአርሶ አደር ኃይል ሊይዝ የሚችል የኢንዱስትሪም ሆነ የአገልግሎት ክፍለ ኢኮኖሚ እንደሌለ በሌላም መልኩ መሬት እንዲሸጥ እና እንዲለወጥ መፍቀድ ውሎ አድሮም ቢሆን የአናሳ ብሔረሰቦችን የማንነት ምልክት ማጥፋትን መፍቀድ እንዲሁም ሕዝቦች እንዲፈናቀሉ ማድረግ እንደሆነ ከአርብቶ አደር አካባቢዎችም ኑሮና ልምድ ጋርም የማይሔድ በመሆኑ ወጥ ፖሊሲ ሊወጣለት የሚያስችል ሁኔታ እንደሌለ በሚገባ ግንዛቤ የተያዘበት ጉዳይ ነበር፡፡

## ክፍል አምስት
## የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም፡ ህብረ-ብሔራዊ ፌዴራሊዝም

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 1

> *"ይህ ሕገ መንግሥት ፌዴራላዊና ዴሞክራሲያዊ የመንግሥት አወቃቀር ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ መንግሥት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በሚል ስያሜ ይጠራል፡፡"*

ይህ ስያሜ ኢትዮጵያ የፌዴራል ሥርዓትን የምትከተል መሆኑን የሚያስረዳ ሲሆን ይህ ድንጋጌ በውስጡ በብዙ መልኩ ሊተነተኑ የሚችሉ የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም መሠረታዊ መርሆዎችና መለያዎችን የያዘ ነው ማለት ይቻላል ፡፡ ይህ አንቀጽ ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ የመንግሥት አወቃቀር መከተል እንዳለባት ይደነግጋል፡፡ ስለዚህ የመንግሥት ሥልጣን በዋናነት ለፌዴራል መንግሥትና ለክልሎች መከፋፈል እንዳለበት የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፌዴራል አወቃቀሩና አሠራሩ ዴሞክራሲያዊ መሆን እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡ በአንቀጽ 1 ሥር የተደነገገውን ከአንቀጽ 45 ጋር አገናዝበን ስናነበው ደግሞ የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ፓርላሜንታዊ ዴሞክራሲ መሆን እንዳለበት በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ በሕገ መንግሥቱ ከተቀመጠው የኢትዮጵያ መንግሥት ስያሜ የምንረዳው ሌላው ጉዳይ የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ሪፐብሊካዊ ፌዴራሊዝም መሆኑን ጭምር ነው፡፡

መንግሥታዊ አወቃቀሩ ንጉሳዊና በዘር ሐረግ ወይም በደም ትስስር ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ላይ የተመሠረተ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

## 5.1. ሕገ መንግሥታዊ ዋስትና ያለው የስልጣን □□□ል መሠረት ያደረገ ፌዴራሊዝም

### 5.1.1. የፌዴራል መንግሥት አወቃቀር፣ ሥልጣንና ተግባር

በ□ዴራል መንግሥትና በክልሎች መካከል የስልጣን ክፍፍል ማለትም የሕግ ማውጣት፣ □ሕፅ ማስ□□ምና የዳኝነት አካላት መኖር እንዲሁም ይህ ክፍፍል ሕገ መንግሥታዊ ዋስትና ያለው ጉዳይ ነው:: እንደሚታወቀው በአሃዳዊ ሥርዓትም ቢሆን ያልተማከለ አስተዳደር ወይም ራስ ገዝ ተብሎ የሚጠራው ዓይነት ሥርዓት ሊኖር እንደሚችል ከሀገራችን ታሪክም ይሁን ከሌሎች ሀገሮች ልምድ ማየት ይቻላል:: ሆኖም ግን በአሃዳዊ ሥርዓት ውስጥ የሚኖረው ያልተማከለ አስተዳደር ከ□ዴራል ሥርዓት የሚለይበት መሠረታዊ ነጥብ በአሃዳዊ ሥርዓት የሚኖረው ያልተማከለ አስተዳደር በማዕከላዊ መንግሥት በጐ ፈቃድና በምክር ቤት አዋጅ የሚሰጥ በመሆኑ ማዕከላዊ መንግሥት ሲፈልግ በአዋጅ ሊሽረው ሊያሰፋው ወይም ሊያጠበው የሚችል በመሆኑ ዋስትና የሌለው ነው::

□□ዴራል ሥርዓት ግን ከዚህ በተለየ መልኩ ከ□ዴራል ሥርዓት ታሪካዊ አመጣጥ □ር በተ□□□ የትኛ□ ስልጣን ለማዕከል የትኛው ስልጣን ደግሞ ለክልሎች ይሰጥ የሚለውን በመወሰን ረገድ ሁለቱም አካላት ማለትም የፌዴራል መንግሥትና ክልሎች በጋራ ተቀምጠው የሚወስኑት ብቻ ሣይሆን ይህ ድርድርና ስምምነት አንደኛው ወገን ብቻ እንደፈለገ እንዳይቀይረው ሕገ መንግሥታዊ ዋስትና □ሰ□□ል:: ስለ□ህም □□ዴራል ሥርዓት ከመጀመሪያው የሁለቱን ወገኖች ድርድርና ስምምነት የሚጠይቅ ሲሆን ከዚያም አልፎ ደግሞ የስልጣን ክፍፍሉ ከነባራዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ማሻሻል ቢያስፈልግ አንደኛው ወገን ብቻውን የሚቀይረው ሳይሆን የሁለቱም አካላት አዲስ ድርድርና ስምምነት የሚጠይቅ ነው:: ለዚህም ነው

በአብዛኞቹ የፌዴራል ሥርዓቶች የኢትዮጵያን ጨምሮ ሕገ መንግሥቶች የበላይና ማሻሻል ሲያስፈልገው ሁለቱንም አካላት ያሣተፈ መሆን እንዳለበት የሚደነግጉት።

በዚህ ነጥብ ዙሪያ በሁለቱም የመንግሥት አካላት መካከል የሥልጣን ክፍፍል መኖርን፣ ይህ የስልጣን ክፍፍልም በሕገ መንግሥት የተካተተ መሆኑን ዋስትና ይኖረው ዘንድም ሕገ መንግሥቱም የበላይ ብቻ ሣይሆን በማሻሻሉ ሂደት ሁለቱንም ያሣተፈ መሆን አለበት።

የማንኛውም ፌዴራሊዝም መሠረታዊ ባህሪይ የመንግሥትን ሥልጣን ለፌዴራል መንግሥትና ለክልሎች ከፋፍሎ መስጠት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም በዚህ ረገድ የተለየ ነገር የለውም፡፡ በዚህ መሠረት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት የፌዴራል መንግሥት እና የክልል መንግሥታት አወቃቀር ሥልጣንና ተግባርን በግልጽ አስቀምጠዋል፡፡ የመንግሥት ሥልጣንም ለፌዴራልና ለክልል መንግሥታት ተከፋፍሏል፡፡ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 1 *"የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በፌዴራል መንግሥትና በክልሎች የተዋቀረ ነው፡፡"* ብሎ ያስቀመጠ ሲሆን አንቀጽ 46/2/ ክልሎች የሚዋቀሩት በሕዝብ አሰፋፈር፣ በቋንቋ፣ በማንነት እና በፈቃድ ላይ በመመስረት መሆኑን ይደነግጋል፡፡

የፌዴራሉ መንግሥትና የክልሎች መንግሥታት ሶስት የመንግሥት አካላት እንደሚኖራቸው በአንቀጽ 50/2/ ተደንግጓል፡፡ እነዚህም የሕግ አውጪ፣ የሕግ አስፈፃሚና የሕግ ተርጓሚ ናቸው፡፡ እያንዳንዳቸው የየራሳቸው ሥልጣንና ተግባር በሕገ መንግሥቱ ተሰጥቷቸዋል፡፡ የፌዴራል ፓርላማ በሁለት ምክር ቤቶች የተዋቀረ ሲሆን እነዚህም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽን

ምክር ቤት ናቸው፡፡ ሁለቱ ምክር ቤቶች የተለያየ አወቃቀር፣ ሥልጣንና ተግባር አላቸው፡፡ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በቀጥታ ነፃና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ በሕዝብ የሚመረጡ ሲሆን የምርጫ መርሆውም አንድ ሰው አንድ ድምጽ የሚለው ነው፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፌዴራል መንግሥት ከፍተኛው ስልጣን አካል ነው፡፡ ሕጐችን ያወጣል፣ የሀገሪቱን ፖሊሲዎች ያወጣል፣ የፌዴራል መንግሥቱ የአስፈፃሚ አካል ርዕሰ መስተዳድር የሆነውን ጠቅላይ ሚኒስትር ይሰይማል፣ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተዋቀረውን የአስፈፃሚ አካል ያፀድቃል፣ የከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናት ሹመት ያፀድቃል፣ አስፈፃሚ አካሉን ይቆጣጠራል፡፡ በሌላ በኩል ሁለተኛው ምክር ቤት የሆነው የፌዴሬሽን ምክር ቤት ለኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ቁልፍ የሆኑ ሚናዎችን ይጫወታል፡፡ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት የሚመረጡት በሁለት አማራጭ መንገድ ነው፡፡ አንዱ በክልል ምክር ቤቶች ሁለተኛው በቀጥታ በሕዝብ የሚመረጡበት ነው፡፡ እንደሚታወቀው ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሀገሪቱ ሉዓላዊ የሥልጣን ባለቤቶች መሆናቸውን አንቀጽ 8 ይደነግጋል፡፡ ስለዚህ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሉዓላዊ የስልጣን ባለቤቶች ወኪል ነው ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህም ነው የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር ከብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብት ጋር የተያያዘ የሚሆነው፡፡ ከፌዴሬሽን ምክር ቤት ስልጣን መካከል ሕገ መንግሥቱን የመተርጐም፣ የሕዝቦች እኩልነትና በሕዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ አንድነት ሥር እንዲሰድና እንዲዳብር ማድረግ ነው፡፡ ይህ ሥልጣን ደግሞ ምክር ቤቱን በእኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተውን የሀገሪቱን አንድነት ጠባቂ ያደርገዋል፡፡ ይህንኑ ለማጠናከር ሲባል በክልሎች መካከል ለሚነሱ

አለመግባባቶች መፍትሔ ያበጅላቸዋል፡፡ በአንቀጽ 39 የተቀመጠውን መብት ለመጠቀም ጥያቄ ቢነሳ በሕገ መንግሥቱ መሠረት ጥያቄውን ይወስናል፡፡ ከዚህ ሌላ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕግ ሊወጣላቸው የሚገቡ የፍትሓ ብሔር ጉዳዮችን ይለያል፤ እንዲሁም የፌዴራሉ መንግሥት ሕገ መንግሥቱ በክልል ሲጣስ ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፡፡ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የክልሎችና የፌዴራሉ መንግሥት የጋራ ተብለው የተመደቡ ገቢዎች በሁለቱ መካከል የሚከፋፈሉበትን እንዲሁም የፌዴራሉ መንግሥት ለክልሎች ድጎማ የሚሰጥበትን ቀመር የመወሰን ሥልጣን አለው፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት ምዕራፍ ስምንት መሠረት የፌዴራል መንግሥት የአስፈፃሚው አካል ጠቅላይ ሚኒስትርና የሚኒስተሮች ምክር ቤት ይኖሩታል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሀገሪቱ ርዕሰ መስተዳድር ሲሆን ፕሬዚዳንቱ ደግሞ የሀገሪቱ ርዕሰ ብሔር ነው፡፡ በፓርላመንታዊ የመንግሥት ሥርዓት ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቁልፍ ቦታ አለው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ አብላጫ መቀመጫ ያገኘው የገዢ ፓርቲ ሊቀመንበር ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ ይሰየማል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስፈፃሚውን አካል ይመራል፡፡ ሌላው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው፡፡ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጠቅላይ ሚኒስትርና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩን እና ሚኒስትሮችን ያጠቃልላል፡፡ ሌሎች ባለሥልጣናትም የዚህ ምክር ቤት አባላት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

የፌዴራል መንግሥት ሶስተኛ አካል የዳኝነት አካል ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት የፌዴራሉም ሆነ የክልል መንግሥታት የዳኝነት አካልን አወቃቀር ሥልጣንና ተግባር በዝርዝር በምዕራፍ ዘጠኝ ደንግጓል፡፡

### 5.1.2. የክልል መንግሥታት አወቃቀር ሥልጣንና ተግባር

የኢ.□.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት የፌዴራል ስርዓቱ መነሻና ሕልውና ከመግቢያውና ከአንቀጽ 8 ለማየት እንደሚቻለው በብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ነፃ ፍላጎት ላ□ □ተመሠረተ እንደሆነና ለፌዴራል መንግሥቱ የተሠጡት ስልጣኖችም አቀራረፃቸው ሲታ□ ተወስነውና ተዘርዝረው የተሰጡ ናቸው:: በሌላ በኩል ተዘርዝረው ያልተሰጡ ስልጣኖች (Residual power) የክልሎች መሆኑ ነው:: ለምሳሌ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 51 ንዑስ ቁዓር /2/ ፣ /3/ የተደነገገውን ያየን እንደሆነ የፌዴራል መንግሥት የሀገሪቱን የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና የልማት ፖሊሲ ስትራቴጂና ዕቅ□ እን□ሚ□□□ □□ል□ል:: ቀዓሉም □ስ□□ማል □ላል:: እነዚህን አንቀጾች በጥሞና ብንመረምራቸውና ቀጥሎም ከአንቀጽ 52 (2)፣ ሐ ጋር ብናስተያያቸው በነዚሁ ለፌዴራል በተሰጡት ስልጣኖችም ቢሆን ፌዴራል መንግሥቱ መሠረታዊ □□ሊሲና የስትራቴጂ አቅጣጫዎች እንዲሁም ደረጃ /standards/ እንጂ ዝርዝር የፖሊሲ ይዘት ያለው መሆን እንደሌለበት ይጠቁማል:: በዚህም ምክንያት ነው ክልሎች በአንቀጽ 52 ስር ለአካባቢያቸው የሚስማማ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የልማት ፖሊሲ መቅረጽ እንደሚችሉ የሚገልፀው:: የሕገ መንግሥቱ አጠቃላይ መንፈስ ማለትም መግቢያውን አንቀጽ 8 እና 39ን ስናይ ክልሎች የፌዴራል ስርዓቱ መስራችና ወሳኝ ኃይል እንደሆኑና እንዲሁም ለፌዴራል መንግሥቱ የተሰጡትን ስልጣናት በማይጋፋ መልኩ የየአካባቢያቸውን የልማት፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ፖሊሲ በመቅረጽ ሰፊ ስልጣን ያላቸው መሆኑን እናያለን::

ስለ□ህም በተለ□□ □ሕገ መንግሥት አንቀጾች ለማየት እንደሚቻለው የክልሎችን ራስን የማስተዳደር መብት ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዳ የሕፅ ማክቀፍ ተካትቶ እናያለን:: ክልሎቹም የራሳቸው የሆነ ምክር ቤት፣ አስፈፃሚና የዳኝነት አካል አዋቅረው እናገኛለን::

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት የፌዴሬሽኑ አባላት 9 ክልሎች እንደሆኑ ይደነግጋል፡፡ እነዚህም የፌዴሬሽኑ አባላት እኩል መብትና ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ የክልል መንግሥት አወቃቀር በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 50/4-7/ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ይህ አንቀጽ ቢያንስ የክልል መንግሥት ሶስቱም የመንግሥት አካላት እንደሚኖሩት በግልጽ አስቀምጧል፡፡ እያንዳንዱ ክልልም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥትን መሠረት ያደረገ የራሱ ሕገ መንግሥት ይኖረዋል፡፡

የክልል ምክር ቤት በክልሉ ሥልጣን ሥር በሆኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት ተለይተው በተቀመጡት ጉዳዮች የክልሉ ሕግ አውጪ አካል ነው፡፡ የክልሉን ሕገ መንግሥት የማዘጋጀት የማጽደቅና የማሻሻል ሥልጣንም የተሰጠው ለዚሁ ምክር ቤት ነው፡፡ ምንም እንኳ የእያንዳንዱ ክልል ምክር ቤት ተግባራት እንደየክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ሊለያይ የሚችል ቢሆንም የክልሉን ሕጎች፣ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች የማውጣትና አፈፃፀማቸውንም የመከታተል ቁልፍ ተግባር በዚህ ምክር ቤት ይከናወናል፡፡

የክልሉ መስተዳድር የክልሉ ከፍተኛ የሕግ አስፈፃሚ አካል እንደሆነ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት በአንቀፅ 50/6/ ይደነግጋል፡፡ ምንም እንኳ

የክልል አስፈፃሚ አካል አወቃቀር ለእያንዳንዱ ክልል የተተወ ቢሆንም የሁሉም የክልል ሕገ መንግሥት የክልሉ መስተዳድር በክልሉ ምክር ቤት የሚሰየም ፕሬዚዳንት እንደሚኖረው ያስቀምጣል፡፡ አባላቶቹም ፕሬዝዳንቱ፣ ምክትል ፕሬዚዳንቱ፣ የቢሮ ኃላፊዎችና ሌሎች በሕግ በሚወሰኑ አባላት መስተዳድር በፌዴራል መንግሥት ደረጃ ባሉት ጠቅላይ ሚኒስትርና የሚኒስትሮች ምክር ቤት የተመሳሳይነት ባሕሪይ አላቸው፡፡ ተጠሪነታቸው ለክልሉ ምክር ቤት ነው፡፡

የክልል የዳኝነት አካል አወቃቀር ሥልጣን ምንም እንኳን የሁሉም ክልሎች ሕገ መንግሥት በድንጋጌዎች ያካተተ ቢሆንም ቀደም ብለን እንዳየነው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ አንቀጽ 50/7/ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት የክልል የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም አንቀጽ 78/3/ ክልሎች የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች፣ የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶችና የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች እንደሚኖራቸው ይደነግጋል፡፡ የክልል ፍርድ ቤቶች የፌዴራሉን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሥልጣን በውክልና ሊወስዱ እንደሚችሉ አንቀጽ 78/2/ እና አንቀጽ 80/4/ /5/ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት ተደንግጓል፡፡

ስለ ክልሎች አወቃቀር ሥልጣንና ተግባር ሲነሳ መታወቅ ያለበት ጉዳይ የኢትዮጵያ ፌዴሬሽን አባላት የሆኑ ክልሎች አወቃቀር ሊለያይ እንደሚችል ነው፡፡ አወቃቀራቸው በዋናነት በክልል ሕገ መንግሥት የሚወሰን መሆኑ ነው፡፡ በዚህ ረገድ አንቀጽ 50/4/ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት ክልሎች አስፈላጊ ሆነው በሚያገኟቸው የአስተዳደር እርከኖች እንደሚዋቀሩ መደንገጉ ይህን ያመለክታል፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ይህን ስለሚፈቅድ ክልሎች

እንደነባራዊ ሁኔታቸው የተለያየ ቅርጽ ያለው መዋቅር እንዳላቸው በተግባር ይታያል፡፡ ለምሳሌ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ ያላቸው መዋቅር እንዲሁም በየደረጃው ያሉት አካላት ያላቸው ስልጣንና ተግባር ከሌሎች ክልሎች ለየት ይላል፡፡ በክልል ደረጃ ሁለት ምክር ቤቶች ያለው ክልል መሆኑን መጥቀስ ይቻላል ፡፡

### 5.1.3. የፌዴራልና የክልል የጋራ ስልጣን በኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት የፌዴራል መንግሥትንና 9 ክልሎችን ያካተተ የመንግሥት አወቃቀር ከደነገገ በኋላ ስልጣናቸውን ለያይቶ ሰጥቷቸዋል ፡፡ ነገር ግን ሕገ መንግሥቱ እያንዳንዳቸው ለብቻቸው ሊኖራቸው የሚችለውን ስልጣን ብቻ ሳይሆን ሁለቱ በጋራ ሊኖራቸው የሚችለውንም ሥልጣን በዝርዝር ያስቀምጣል፡፡ የፌዴራሉና የክልል የጋራ ሥልጣን በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት የተደነገገው በተለይ ከታክስና ከግብር ሥልጣን ጋር በተያያዘ ነው፡፡ እነዚህ የጋራ ሥልጣኖች በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 98 በግልፅ ተዘርዝረዋል፡፡ እነዚህም የጋራ ስልጣኖች የሚከተሉት ናቸው:-

- የፌዴራል መንግሥትና ክልሎች በጋራ በሚያቋቁሚቸው የልማት ድርጅቶች የልማት ላይ የንግድ ትርፍ ግብር የስራ ግብር የሽያጭና የኤክሳይዝ ታክስ በጋራ ይጥላሉ ይሰበስባሉ፡፡
- በድርጅቶች የንግድ ትርፍ ላይና በባለ አክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብር የሽያጭ ታክስ በጋራ የጥላሉ ይሰበስባሉ፡፡

- በከፍተኛ የማዕድን ስራዎችና በማናቸውም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች ላይ የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎችን በጋራ ይጥላሉ ይሰበስባሉ፡፡

እነዚህ በጋራ ለፌዴራሉ መንግሥትና ለክልሎች የተሰጡ ስልጣኖች ሲሆኑ በሕገ መንግሥቱ ለፌዴራሉ መንግሥት በተለይ ወይም ለፌዴራሉ መንግሥትና ለክልሎች በጋራ በግልፅ ያልተሰጠ ስልጣን የክልል ስልጣን እንደሚሆን አንቀጽ 52/1/ ይደነግጋል፡፡

በአንቀፅ 99 መሰረት በዚህ ሕገ መንግሥት ተለይተው ያልተሠጡ ታክስና ግብር የመጣል ሥልጣኖች በሚመለከት የፌዴሬሽኑ ምክር ቤትና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጋራ ስብሰባ በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ይወስናሉ፡፡

## 5.2. ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦችን መሠረት ያደረገ ፌዴራሊዝም

የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም መሠረታዊ መርህ ሕብረ ብሔራዊ የፌዴራል ሥርዓትን ማስፈን ነው ፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ሕብረ ብሔራዊነት በሕገ መንግሥታችን ከመግቢያው ጀምሮ ተንፀባርቋል፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት መግቢያ *"እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች... ይህ ሕገ መንግሥት ከዚህ በላይ ለገለጽናቸው ዓላማዎችና እምነቶች ማሰሪያ እንዲሆነን ... ዛሬ ኅዳር 29 ቀን 1987 አጽድቀነዋል"* በሚል ይጀምራል፡፡ ሕገ መንግሥቱ ቀጥሎ ስለ ሕዝብ ሉዓላዊነት ሲደነግግ *"የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ እና ሕዝቦች የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤቶች"* መሆናቸውን፣ በተጨማሪም *"ይህ ሕገ መንግሥት የሉዓላዊነታቸው መግለጫ"* መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ በአንቀጽ 8 ላይ ያስቀምጣል፡፡

ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሉዓላዊ ስልጣን ባለቤት ናቸው ብሎ ማስቀመጡ ሀገሪቷ የምትከተለው ፌዴራሊዝም መለያ ባሕሪይ እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡ በተለይ የሀገራችን የፌዴራሊዝምና ፌዴራላዊ የመንግሥት ቅርጽ በአንቀጽ 45 - 48 በተደነገገው መልኩ ለመቀመጡ በአንቀጽ 8 የሉዓላዊነት ሥልጣን ውጤት ነው ማለት ይቻላል፡፡ በአንቀጽ 39 ሥር የተደነገገው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብትም የዚሁ ሉዓላዊነት ውጤት መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከአንቀጽ 46 - 47 የተደነገገው ድንጋጌ የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝምን ህብረ ብሔራዊነት ቁልጭ ባለመልኩ አስቀምጧል፡፡

ሕገ መንግሥቱ በተለይ በአንቀፅ 39 ላይ ለብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብት ከፍተኛ እውቅና ሰጥቷል፡፡ ሕገ መንግሥቱ ማንኛውም ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰንና አይስማማኝም በሚልበት ወቅትም የራሱን መንግሥት ሊመሠርት እንደሚችል በማያሻማ መልኩ ደንግጓል፡፡ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 39 ላይ የብሔሮችን፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን መብት በተመለከተ የሚከተሉት ተደንግገዋል፡፡

/1/ ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል ያለው መብቱ በማንኛውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነው፡፡

/2/ ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ ራሱን የማስተዳደር ሙሉ መብት አለው፡፡ ይህ መብት ብሔሩ፣ ብሔረሰቡ፣ ሕዝቡ በሰፈረበት መልክዓ ምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋም፣ እንዲሁም

በክልልና በፌዴራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብትን ያጠቃልላል፡፡

ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 39/5/ በግልጽ የተገለፀ ሲሆን ይኸውም *ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ ማለት "ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባሕል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑ የሥነ ልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያየዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ ናቸው"* በሚል ይገልፀዋል፡፡

በሕገ መንግሥቱ እውቅና የተሰጣቸው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብቶች በሕገ መንግሽቱ ላይ ብቻ ተጽፈው የቀሩ ሳይሆን ተግባራዊ እየሆኑ ያሉ መብቶች ናቸው፡፡ በሀገሪቱ የሚገኙ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በቋንቋቸው የመማር፣ የመዳኘት፣ ባሕላቸውን የማሳደግና ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብቶችን በማጣጣም ላይ የሚገኙ ሲሆን ከሌሎች ጋር ባሉ ግንኙነቶችም ባሕሎቻቸውና እኩልነታቸውም ተረጋግጧል፡፡ በተለይም ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በመሠረቷቸው ክልሎች ራሳቸውን በራሳቸው ስለሚያስተዳድሩ ባሕሎቻቸውን ለማበልፀግ አመቺ ሁኔታ እንደተፈጠረላቸው መገመት አያስቸግርም፡፡ ለዚህም ነው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 25 *"ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው፤ በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በቀለም በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ*

*ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው"* በሚል የተደነገገው፡፡

እንዲሁም በሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 27 የሃይማኖት፣ የእምነትና የአመለካከት ነፃነትን በተመለከተ *"ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የሕሊና እና የሃይማኖት ነፃነት አለው፡፡ ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ ወይም የመቀበል፣ ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ የማስተማር ወይም የመግለጽ መብትን ያካትታል"* በሚል ሰፍሯል፡፡ ይህ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ለብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም ለግለሰቦች የመብት ጥበቃ ከፍተኛ ዋስትና የሚሰጥ ነው፡፡

ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው ከማስተዳደር ባሻገር በፌዴራል ደረጃም ሚዛናዊ በሆነ ውክልና እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ በፌዴራል ደረጃ የተመጣጠነ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ውክልና በሕግ አውጪው አካል ውስጥ ብቻ ሳይሆን በሕግ አስፈፃሚውና ሕግን በሚተረጉመውም ጭምር የተጠበቀ ነው፡፡ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የተመጣጠነ ውክልና በሕግ አውጪው አካል ውስጥ እንዲኖር ለማድረግ የምርጫ ወረዳዎችን ለዚሁ በሚያመች መልኩ ከማደራጀት ባሻገር አፈፃፀሙን በምርጫ ሕጉ ላይ በዝርዝር እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡ በሕገ መንግሥቱም በፌዴራል መንግሥት ደረጃ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ቁጥር የሕዝብ ብዛትንና በልዩ ትኩረት ውክልና የሚሰጣቸው የአናሳ ብሔረሰብ ሕዝቦችን ቁጥር መሠረት በማድረግ ከ550 የማይበልጥ ሆኖ ከዚህ ውስጥም አናሳ ብሔረሰቦች ከ20 የማያንስ

መቀመጫ እንደሚኖራቸው በአንቀጽ 54/3/ ላይ ተደንግጓል፡፡ ይህም የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚዛናዊ የሆነ ውክልና ያላቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በፌዴሬሽን ምክር ቤት እያንዳንዱ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ ቢያንስ አንድ ተወካይ ይኖረዋል በተጨማሪም የብሔሩ፣ ብሔረሰቡ ወይም ሕዝቡ አንድ ሚሊዮን ሕዝብ ተጨማሪ አንድ ተጨማሪ ተወካይ እንደሚኖረው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 61/2/ ተደንግጓል፡፡ ይህም በፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና መኖሩንና እያንዳንዱ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ በሁለቱም የፌዴራል ምክር ቤቶች ተወካይ እንዲኖረው በማድረግ ሁሉም ሰፊ ሀገራዊ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የማይገደብ መብት መጐናፀፋቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

## 5.3. የራስን ዕድል በራሱ የመወሰን መብትን መሠረት ያደረገ ፌዴራሊዝም

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 1 *"ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ያለው መብቱ በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነው፡፡"* በሚል ተደግጓል፡፡ ይህም በመሆኑ የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም የሚፈቅደው በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ አንድነትን ነው፡፡ ከዚህ በፊት የነበረው አስገዳጅ አንድነት በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ቦታ የሌለው መሆኑን ያረጋገጠ ፌዴራሊዝም ነው፡፡ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች መብት ሲነሳ መብቱ የራስን ዕድል በራስ መወሰን የሚለውን ቁልፍ መርህ ተንተርሶ የሚዘረዝር ነው፡፡ የራስን ዕድል በራስ መወሰን በማንነት በቋንቋ፣ በባሕል፣ በታሪክ፣ በአስተዳደር ይገለፃል፡፡ በሕገ

መንግሥቱ አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 2/3 እና 4 ላይ እያንዳንዱ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ ቋንቋውን የመናገር፣ የመጻፍ እና ቋንቋውን የማሳደግ መብቱ የተረጋገጠ ነው፡፡ እንዲሁም ባሕሉን የመግለጽ፣ የማዳበርና የማስፋት ታሪኩንም የመንከባከብ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ራስን የማስተዳደር መብት በልዩ ልዩ መልክ ይገለፃል፡፡ በመጀመሪያ ሕዝብ በሰፈረበት መልክዓ ምድር መንግሥታዊ ተቋማትን በማዋቀር ራሱን ያስተዳድራል፡፡ ከዚህ አልፎ ደግሞ በክልልና በፌዴራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብቱ ይገለፃል፡፡ የራስን ዕድል በራስ መወሰን የመጨረሻ መልኩ እስከ መገንጠል ያለውን መብትም የሚያጠቃልል ነው፡፡ ሕገ መንግሥቱ ለዚህ መብት በጊዜ ሰሌዳ የተደገፈ ዝርዝር ሥነ ሥርዓት በመደንገግ አሠራሩን በግልጽ አስቀምጦታል፡፡

## 5.4. በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ አንድነትን መሠረት ያደረገ ፌዴራሊዝም

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በጋራ መፈቃቀድና በሕግ የበላይነት የተመሠረተ አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ ለመመስረት ቃል የገቡት የቃል ኪዳን ማሰሪያና የጋራ መተዳደሪያቸው የሆነውን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት በማጽደቅ ነው፡፡ ሕገ መንግሥቱ የሉዓላዊነታቸው መገለጫ ነው፡፡ ስለሆነም ሕገ መንግሥቱንና ሕገ መንግሥታዊ ስርዓቱን በማክበር ልዩነቶች በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ የሚፈቱበትን ሥርዓት በሕገ መንግሥቱ በበቂ ሁኔታ ዘርግተዋል፡፡ ከዚህ ውጪ የሚደረግ ማናቸውም አፍራሽ እንቅስቃሴ በሀገር ሕልውና ላይ እንደተቃጣ ጥቃት መታየትና የዚህ ዓይነት አፍራሽ ድርጊት በሕግ አግባብ የመቆጣጠርና የመከላከል ሕገ መንግሥታዊ ኃላፊነት የሁሉም አካላት መሆኑን በውል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም የመተባበር ፌዴራሊዝም (co-operative federalism) መሆኑን የሚያንፀባርቁ አያሌ ድንጋጌዎችን በኢ.ፌዴ.ሪ ሕገ መንግሥት እናገኛለን እንዲሁም ሌሎች የመተጋገዝ ሁኔታዎችን በማየት መረዳት እንችላለን፡፡

በሕገ መንግሥቱ መግቢያ የተዘረዘሩት ከላይ የተጠቀሱት ቁም ነገሮች የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ሕብረ ብሔራዊ ብቻ ሳይሆን የመተባበር ፌዴራሊዝም መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ የፌዴራሊዝም መርህ በፌዴራልና በክልሎች መካከል መኖር የሚገባውን ግንኙነት ብቻ ሳይሆን በክልሎች መካከል መኖር የሚገባው ግንኙነት የመተባበርና የመደጋፍ ግንኙነት መሆን እንዳለበት የሚያሳይ ነው፡፡

በኢትዮጵያ የመተባበር ፌዴራሊዝም በዚህ ብቻ አያበቃም፡፡ የሕገ መንግሥቱ የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች መካከል "መንግሥት በእድገት ወደኋላ ለቀሩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ልዩ ድጋፍ ማድረግ እንዳለበት" አንቀጽ 89/4/ በግልጽ ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሠረት የፌዴራል መንግሥት በማደግ ላይ ላሉት ክልሎች የሚያደርገው ልዩ ድጋፍ የዚህ የመተባበር ፌዴራሊዝም መገለጫ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ ክልል ከክልል የሚያደርጉት ትብብሮችም የመተጋገዝ ፌዴራሊዝም መገለጫ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በአፋርና በትግራይ ክልሎች እንዲሁም በአፋርና በአማራ ክልሎች በቤንሻንጉል/ጉሙዝና በአማራ ክልሎች እንዲሁም በኦሮሚያና በሱማሌ ክልሎች መካከል የተደረጉትና እየተደረጉ ያሉት የመተጋገዝ ሥራዎች የኢትዮጵያን የመተባበር ፌዴራሊዝም የሚያንፀባርቁ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የፌዴራል መንግሥት

ለክልሎች ከሚሰጠው የድጐማ በጀት ከታዳጊ ክልሎች በአንፃራዊ ሁኔታ ሻል የሚሉት ክልሎች ለአራቱ ታዳጊ ክልሎች ከድርሻቸው አንድ በመቶ (1%) የሚሆን በጀት እንዲሰጥ መወሰናቸው ሌላው የመተባበር ፌዴራሊዝም ማሳያ ነው፡፡

## 5.5. የተለየ የሕገ መንግሥት ትርጉም ሥርዓት የዘረጋ ፌዴራሊዝም

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሥርዓት የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄን በተመለከተ ለየት ያለ በፈጠራ ችሎታ የዳበረ አወቃቀርና አሠራር ዘርግቷል፡፡ ጉዳዩን ከነምክንያቱ መገንዘቡ ተገቢ ይሆናል፡፡ በመጀመሪያ የሕገ መንግሥቱ ተርጓሚ ማን ነው ለሚለው ቀጥተኛ ጥያቄ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሕገ መንግሥቱን የመተርጎም ሥልጣን ይኖረዋል በማለት የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 62 ንዑስ አንቀጽ (1) መልስ ሰጥቷል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን አንቀጹ ከምክር ቤቱ ሥልጣኖች ሕገ መንግሥትን መተርጎም ዋንኛና በመጀመሪያ ደረጃ የሚቀመጥ ሥልጣንና ኃላፊነት በማድረጉ የፌዴሬሽን ምክር ቤቱ ሕልውናውና ተልዕኮው በተለየ ሁኔታ ከሕገ መንግሥቱ ጋር የተሳሰረ መሆኑን በግልጽ ያስቀምጣል፡፡

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሕገ መንግሥቱን በሚተረጉምበት ጊዜ አሠራሩ ምን መሆን እንዳለበት ሕገ መንግሥቱ በአንክሮ ያሰበበት ጉዳይ በመሆኑ ስልጣንና ተግባሩን በሚዘረዝረው ድንጋጌው ውስጥ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔን ያደራጃል በማለት ይደነግጋል፡፡

የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አወቃቀር እና ሥልጣንና አሠራርን በተመለከተ ሕገ መንግሥቱ ስለ ፍርድ ቤቶች አወቃቀርና ሥልጣን ባስቀመጠው የሕገ መንግሥቱ ምዕራፍ ዘጠኝ በሶስት ልዩ ልዩ አንቀጾች

ተደንግጓል፡፡ ስለዚህ ሕገ መንግሥቱ ስለ ሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የሚደነግገውን በጥሞና ማየቱ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በሕገ መንግሥቱ በፍርድ ቤቶች አወቃቀርና ሥልጣን ምዕራፍ ውስጥ መዘርዘሩ ጉባዔው በጠባዩ ከሌሎች መንግሥታዊ አካላት ይልቅ ከፍርድ ቤቶች ጋር ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን የሚያንፀባርቅ ነው፡፡

ይህ ጉባዔ በሕገ መንግሥቱ የተቋቋመና እውቅና ያገኘ አካል በመሆኑ ሥልጣኑንና ተግባሩን በጥንቃቄ መወጣት ይኖርበታል፡፡ የጉባዔው አባላት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ (2) ላይ እንደተቀመጠው አሥራ አንድ ሲሆኑ እነርሱን በሶስት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ የጉባዔው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ሲሆኑ፣ የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ከአባላቱ መካከል የሚወክላቸው ሶስት ሰዎች ደግሞ የጉባዔው አባላት ሆነው ያገለግላሉ፡፡ የተቀሩት ስድስት የጉባዔው አባላት በሙያ ብቃታቸውና በሥነ ምግባራቸው የተመሰከረላቸው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅራቢነት በሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት የሚሾሙ መሆናቸው በአንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ (2ሐ) ተደንግጓል፡፡ ይህ የጉባዔው አባላት ቅንጅት ልዩ ልዩ የመንግሥት አካላትን የሚያሳትፍ ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ሲወከሉ፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ከአባላቱ መካከል ሶስት ሰዎች በመምረጥ በጉባዔው ውስጥ ይወከላል፡፡ እንዲሁም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለስራው ብቁ የሆኑትን ሰዎች አጭቶ በሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት እንዲሾሙ ያቀርባል፡፡ ስለዚህም የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ

ጉባዔ አወቃቀር የፍርድ ቤቶች፣ የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት የጋራ ኃላፊነት ነው፡፡

የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባርን በተመለከተ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 84 በአራት ንዑስ አንቀጾች ተደግጓል፡፡ ዋናው የጉባዔው ሥልጣን ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን ማጣራት ነው፡፡ ይህ ማለት ማንኛውም ሕገ መንግሥታዊ ጉዳይ በጉባዔው ማለፍና መጣራት ይኖርበታል፡፡ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳይን የማጣራት ሂደት ሁለት አማራጭ ውጤቶች ይኖሩታል፡፡ አንደኛው ሕገ መንግሥቱን መተርጎም የሚጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ሕገ መንግሥቱን መተርጎም የማያሳፈልግ መሆኑን መወሰን ነው፡፡ ሕገ መንግሥቱ መተርጎም ይኖርበታል ብሎ ጉባዔው ከወሰነ በጉዳዩ ላይ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፡፡ የፌዴሬሽን ምክር ቤትም የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በሚያቀርብለት ሕገ መንግሥታዊ ጉዳይ ላይ በ30 ቀናት ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡ ይህ በፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚሰጥ ውሳኔም የመጨረሻ ነው፡፡

## 5.6. የሕገ መንግሥት መሻሻል ሥርዓትን የዘረጋ ፌዴራሊዝም

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሥርዓት የፌዴራል ሥርዓቶች ጠቅላላ መርህን በመከተል የሕገ መንግሥትን መሻሻል በተመለከተ በአንቀጽ 104 እና 105 ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የሕገ መንግሥቱን አንቀጾች የማሻሻል ሀሳብ ከፌዴራል መንግሥትም ሆነ ከክልል መንግሥት ሕግ አውጪ አካላት ሊመነጭ ይችላል፡፡ ከክልል መንግሥታት የሚመነጭ ከሆነ የሕገ መንግሥቱን ማሻሻያ ሀሳብ ከፌዴሬሽኑ አባል ክልሎች ውስጥ አንድ ሶሰተኛው የክልል ምክር ቤቶች በድምጽ ብልጫ

የደገፉት መሆን ይኖርበታል፡፡ ከፌዴራል መንግሥት የሚመነጭ ሲሆን የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሀሳብ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ የደገፈው እንዲሁም የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ የደገፈው መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በኋላ ነው የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሀሳብ ለውይይትና ለውሳኔ ለመላው ሕዝብና የሕገ መንግሥቱ መሻሻል ለሚመለከታቸው ክፍሎች የሚቀርበው፡፡

ሕገ መንግሥታችን የሕገ መንግሥት መሻሻል ሂደትን በሁለት ክፍሎ የሚያይ ሲሆን አንደኛው የሕገ መንግሥት መሻሻል በሕገ መንግሥቱ ምዕራፍ ሶስት የተዘረዘሩትን መብቶችና ነፃነቶችን እንዲሁም አንቀጽ 104ን የማይመለከት የሕገ መንግሥት መሻሻል ሂደት ነው፡፡ ይህን መደበኛ የሕገ መንግሥት መሻሻል ሂደት ልንለው እንችላለን፡፡ ሁለተኛው የሕገ መንግሥት መሻሻል ሂደት በምዕራፍ ሶስት የተዘረዘሩትን መብቶችና ነፃነቶችን በሙሉ ያጠቃልላል፡፡ በተጨማሪም አንቀጽ 104ን የሚሸፍን ነው፡፡ ይኸኛው ልዩ የሕገ መንግሥት መሻሻል ሂደት ልንለው እንችላለን፤ ልዩ የሕገ መንግሥት መሻሻል ሂደት ከመደበኛው የሚለየው ሥርዓቱ የድምጽ ሰጪውን ቁጥር ከፍ በማድረጉ ነው፡፡ ይህንንም ያደረገበት ምክንያት መብቶችና ነፃነቶች በቀላሉ እንዳይሸረሸሩ ነው፡፡

መደበኛ የሕገ መንግሥት መሻሻል ሂደት ከሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሀሳብ ማመንጨት ተነስቶ ውሳኔ የሚያገኘው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በጋራ ስብሰባ በሁለት ሶስተኛው ድምጽ የቀረበውን

ማሻሻያ ሲያፀድቁና ከፌዴሬሽኑ አባል ክልሎች ምክር ቤቶች ውስጥ የ2/3ኛ ክልሎች ምክር ቤቶች በድምጽ ብልጫ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያፀድቁት ነው፡፡

መብቶችና ነፃነቶችን እንዲሁም የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሃሳብን ማመንጨት የሚመለከት ልዩ የሕገ መንግሥት መሻሻል ሂደት ሁሉም የፌዴሬሽኑ አባል ክልሎች ምክር ቤቶች የቀረበውን ማሻሻያ በድምጽ ብልጫ ማጽደቅ ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት እያንዳንዳቸው የቀረበውን ማሻሻያ በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲያፀድቁት ነው፡፡

በአጠቃላይ ዘመናዊ ፌዴራሊዝም በሰው ልጅ ታሪክ አዲስ ዓይነት የመንግሥት አወቃቀር ሲሆን፣ ዛሬ የዓለም ሲሶ መንግሥታት የሚጠቀሙበት መንግሥታዊ አሠራር ነው፡፡ አንድን መንግሥት ፌዴራል የሚያሰኘው ሕገ መንግሥታዊ የሥልጣን ክፍፍል ሲኖረው ብቻ ነው፡፡ የፌዴሪሊዝም የሂሳብ ስሌቱም አንድና አንድ ሲደመር ሶስት ይሆናል ወደሚለው መደምደሚያ ያደርሳል፡፡ ሕገ መንግሥታዊ የሥልጣን ክፍፍልም ከታች ወደ ላይም ይሁን ከላይ ወደታች በተዋቀረ ፌዴራል ሥርዓቶች ልዩ ጠባይ ሲሆን፣ አንደኛው ቤት በተለይ የፌዴራል ሥርዓቱን ሁኔታ የሚያንፀባረቅ ይሆናል፡፡ ሕገ መንግሥቱን መተርጎም በፌዴራል ሥርዓቶች ልዩ ትኩረት የሚሰጠው መሆኑም የማይታለፍ ጉዳይ ነው፡፡

ወደ ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሥርዓት መርሆዎች ስንመጣ ትልቁ ጉዳይ ኢትዮጵያ የብሔረሰባዊ ፌዴራሊዝምን መርሆ መከተልዋን ነው፡፡ ይህንንም መርህ ተግባራዊ በማድረግ ለዘመናት ተንሰራፍቶ የቆየውንና ሲያበጣብጥ የኖረውን

የብሔረሰብ ጥያቄ ለአንዴና ለመጨረሻ ምላሽ በመስጠት የኢትዮጵያ ሕዝቦች በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ በጋራ ለመገንባት ቆርጠው መነሳታቸውን የሚገለጽ ነው፡፡ ይህ የብሔረሰባዊ ፌዴራሊዝም መርህ ሲዘረዘር የብሔረሰብ እኩልነትን ብቻ ሳይሆን፣ የቋንቋ የሃይማኖት የፆታ እኩልነትን የሚያራምድ እና የስብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበርን የሚያረጋግጥ መሠረታዊ መርህ ነው፡፡ የሕገ መንግሥት የበላይነትን የሚደነግግ መርህ በመሆኑም ለሕገ መንግሥት ትርጉም ጉዳይ ለየት ያለ ትኩረት የሚሰጥ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሥርዓት የሕገ መንግሥት ትርጓሚ አካል የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሲሆን፣ ምክር ቤቱም ኃላፊነቱን የሚወጣው በአሰያየሙ ልዩ ልዩ አካላት በተካፈሉበት በሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በመታገዝ ነው፡፡

በመጨረሻም የፌዴሬሽኑን ሕገ መንግሥት ማሻሻል ሲያስፈልግ የፌዴሬሽኑ አባላት የሆኑ መንግሥታት ሁሉ የሚካፈሉበት ሥርዓት መሠረት መሆኑ ነው፡፡

# ክፍል ስድስት
## ማጠቃለያ

በኢትዮጵያ የተፃፈ ሕገ መንግሥት ሥራ ላይ መዋል ከጀመረበት ከ1923 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1983 ዓ.ም. ድረስ የተለያዩ ሕገ መንግሥቶች ሥራ ላይ ውለዋል:: ሆኖም አንዳቸውም ቢሆኑ ለኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መሠረታዊ ጥያቄ ምላሽ የሰጡ አልነበሩም፡፡ በንጉሣዊው ሥርዓት ስራ ላይ ውለው የነበሩት ሕገ መንግሥቶች የንጉሠ ነገሥቱን ስልጣን ሕጋዊ ለማድረግና የፊውዳላዊውን አገዛዝ እድሜ ለማራዘም ታስበው የተቀረጹና የጸደቁ ነበሩ፡፡ በውጤታቸውም ሀገሪቱ ለኋላ ቀርነት፣ ለረሀብና ለችግር እንዲሁም ሕዝቧን ለስደት ዳርገዋል፡፡

ደርግ ወደ ስልጣን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ የሕዝብን ሉዓላዊነትና የስልጣን ባለቤትነት በመንጠቅ፣ የዜጐችን የመናገርና ሃሳብን በነፃ የመግለጽ፣ የአመለካከት ነፃነትን፣ የመደራጀትና ማሕበር የመመስረት፣ በሕይወት የመኖርና፣ ኢ-ሰብዓዊ ከሆነ አያያዝ የመጠበቅ ነፃነትን በግልጽ የሚጥሱ በርካታ ተግባራትን ፈጽሟል፡፡ በዚህ ድርጊቱ በወቅቱ የነበረውን ትውልድ ያለፍርድ በመግደልና ኢ-ሰብዓዊ ለሆነ እስር በመዳረግ አሰቃቂ ወንጀሎችን ፈጽሟል፡፡ በ1980 ዓ.ም "የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት" በሚል ስያሜ ለይስሙላ ያፀደቀው ሕገ መንግሥት ሕዝብ ሳይመክርበትና የሕዝብን ጥያቄ መሠረት ያላደረገ በመሆኑ ሥርዓቱ የነበረውን ችግር ይበልጥ በማባባስ ሀገሪቱን ወደ ማትወጣበት አዘቅት ውስጥ ከቷት አልፏል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት በሀገሪቱ ውስጥ ዘላቂ ሰላም ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ እንዲሰፍን የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መሠረታዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚያስችል ዘመናዊ አስተሳሰብ ይዞ የተነሳ ሰነድ መሆኑን አይተናል፡፡ በሕገ መንግሥቱ የተዋቀረው ፌዴራላዊ ሥርዓት በብሔራዊ ማንነት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ የፌዴራል ሥርዓቱ ዓላማ በፍቃደኝነት አብሮ መኖር ሆኖ ፍቃደኝነት ከሌለ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 39 በተደነገገው መሠረት እስከመገንጠል ድረስ ያለው መብቱ በማያሻማ ሁኔታ መቀመጡ ሕገ መንግሥታችን ዘመናዊ አስተሳሰብ የያዘ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን እንዲሁም የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ምክር ቤት የሆነው የፌዴሬሽን ምክር ቤት መቋቋም በስያሜው፣ በአወቃቀሩ፣ በአሰራሩና በስልጣን ድርሻው ከብዙዎች የላይኛው ምክር ቤቶች በተለየ ሁኔታ የተዋቀረ መሆኑን አይተናል፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ብሔረሰባዊ ፌዴራሊዝምን መርሆ አድርጎ የተቋቋመና ይህንንም መርህ ተግባራዊ በማድረግ ለዘመናት ተንሰራፍቶ የቆየውንና ሀገሪቱን ሲያበጣብጥ የኖረውን የብሔር ጥያቄ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ምላሽ ሰጥቶ ሕዝቦች በነፃ ፍላጐትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ በጋራ የመገንባት ሕልማቸውን እውን በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

ይህ የፌዴራል ሥርዓት በኢትዮጵያ መተግበር የጀመረው ከኅዳር 29 ቀን 1987 ዓ.ም. ጀምሮ በመሆኑ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች በሕገ መንግሥታችን መግቢያ ላይ ያስፈሯቸውን ዓላማዎች ከግብ በማድረስ ሂደት ጅምር ላይ በሂደቱም ብዙ ትምህርት እየቀሰምን አሠራራችንን እያሻሻልንና እያጠናከርን ግባችንን እንደምንመታ፣ የኢትዮጵያ የወደፊቱ ዕድልም ብሩህ

ተስፋ የሚሰጥ መሆኑን ከጅምሩ ማየት የሚያስችል መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## ªቢ. ጽሑፎች


- ፋሲል ናሆም (ዶ/ር)፣ *የፌዴራሊዝም ጽንሰ ሃሳቦችና የኢትዮጵያ የፌዴራል ሥርዓት አወቃቀር መርሆዎች /ጥቅምት 1991/*
- Fasil Nahom, Constitution for a Nation of Nations: The Red Sea Press, Inc.1997
- ፋሲል ናሆም (ዶ/ር)፣ *የሀገራችን ፌዴራሊዝም ልዩ ባህሪያትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በኢትዮጵያ* መስከረም 2002 ዓ.ም
- Hashim Tewfik, (Dr.) Transition to Federalism: The Ethiopia Experience. March 20, 2010
- ሀሺም ቶፊቅ (ዶ/ር)፣ ሕብረ ብሔራዊነትና ሃገራዊ ግንባታ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት ኅዳር 2000 ዓ.ም
- የፌዴራል የፍትሕ አካላት ባለሞያዎች የስልጠና ማዕከል ማንዋል /1999/
- በኢ. ፌ. ዴ. ሪ.የፌዴሬሽን ምክር ቤት የተዘጋጀ የስልጠና ሰነድ /2003/
- የ1923 ዓ.ም ሕገ መንግሥት
- የ1948 ዓ.ም ሕገ መንግሥት
- የ1980 ዓ.ም ሕገ መንግሥት
- አዋጅ ቁጥር 31/67 እና 47/67
- የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ቻርተር
- የ1987 ዓ.ም የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት
- የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ጉባዔ ቃለ ጉባኤዎች /ከጥራዝ 1 - 6/